ሰማያዊ ፈረስ
አዘጋጅና አቅራቢ / ሰራዊት ፍቅሬ
ደራሲ / ሰራዊት ፍቅሬ
ኮከብ ተዋኒ / ሰራዊት ፍቅሬ

ገምጋሚ /ፓስወርድ

መግቢያ

ስለ ሰማያዊ ፈረስ አስተያየት ከሰጡ ተዋኒያን መሀል አንዱ 'ሰራዊት ፍቅሬ በፊልሙ አባይን ማነጋገር ችሎአል ' በማለት አድንቆታል። የካስትሮ ምስክር ቸጉቬሮ ካልሆነ .

ከተመልካችም እንዲሁ በጎና ቀና አስተያይት የሰጡትን ያህል የነቀፋም አይጠፋም። የፊልም አሰራር ጥበብን መሰረት ባደረገ መልኩ ፊልሙን የገመገመ ጽሁፍ ግን እስካሁን አላነበብኩም።

ግምገማ በተለይም የፊልሙን ድክመት አጉልቶ የሚያሳይ ከሆን በፊልም ሰሪው አካል በኩል በበጎ አይታይም።
ይህ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት ግልጽ ይመስለኛል። ሰማያዊ ፈረስን የሚያክል ፊልም ለመስራት የሚጠይቀው መስተዋጽኦ ቀላል አይደለም። የፊልም ጥባብን የሚያራምድ መሬት ባልተደላደለበት ወቅትና ቦታ ከስክሪፕት እስከ ስክሪን ያለውን እልህ አስጨራሽ ጉዞ በሚገባ አጠናቆ ፊልምን ለህዝብ ማቅረብ ጊዜ፣ ጉልበትና በጭካኔ የተጠራቀመችውን ወይም በስንት ደጅ ጥናት የተገኘችን የብድር ገነዘብ የሚያሙዋጥጥ በጣም ከባድ ስራ ነው። ይህን በመገንዘብ ገምገሚዎችና ሀያሲዋች ከነቀፋና አሉታዊ ትችት ከመሰንዘር ይታቀባሉ። የፊልሙ አቅራቢዎች ያወጡት ወጭ፣ የተበደሩት ገንዝብ፣ የፊልም ሰራተኞችና ተዋንያን ድካም፣ የልዩ ልዩ እቃና ቦታ ኪራይ ሳይከፈል ፊልሙን ከገበያ ውጭ ሊያደርግ የሚችል ማንኛውም ነገር በጥንቃቄ መሆን አለበት። ይህን ከባድ ጉዞ ጨርሰው እንደገና ሌላ ፊልም ለመስራት በቂ ቀሪ ሃሞት የሚኖራችው እንደነ ሰራዊት ፍቅሬና የቀዝቃዛ ወላፈን ደራሲና አዘጋጅ፣ ቴዎድሮስ ተሾመ ዓይነቶች ብርቱ ሰዎች ብዙ አይመስሉኝም። ስለሆነም የሚገባቸው የሞራልና የፊይናንስ ድጋፍ ሊጉዋደል አይገባም። ይህን የምናደርገው በሁለት ቀላል መንገዶች ነው።

፩ኛ ፊልማቸውን በመግዛትና በማየት
፪ኛ ፊልማቸው ኮፒ ሆነ ሲሸጥ፣ ሻጪን ለህግ በማጋለጥ።

በተረፈ ሰማያዊ ፈረስ አሁን ለህዝብ በነጻ የተለቀቀ ስለመሰለኝ፣ ፊልሙን ከተለያይ መአዘን በመመልከት ግምገማዬን አቀርባለሁ። ግምገማው ከእንግዲህ በፊልሙ ገበያ ላይ የሚኖረው ጫና ሚዛን የሚደፋ አይሆንም። ከደፋም ገበያውን እንደገና የሚቀሰቅስ ነው የሚሆነው , ብዬ አምናለሁ ።

ግምገማን ከሂስ ጋር የሚያምሳስሉ አሉ። በኔ እምነት ግን ሁለቱ የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው። ሂስ የግል አስተያይት ሲሆን ግምገማ በተወሰነ መስፈርት፣ አሰራርና ልምድ ላይ ተመስርቶ፣ የማሻሻ አማራጭ እያሳየ የሚቀርብ ትንተና ነው። ከዚህ በታች የማቀርበው አስተያየት የግምገማ ስልት የተከተለ ይሆናል። አላማዬ በአገራችን የሚሰሩ ፊልሞች ጥራት እንዲጠበቅ የበኩሌን ለማለት ያህል እንጂ የአንድን ፊልም ስራ ለማወደስ ወይም ለማጣጣል አይደለም። ሰማያዊ ፈረስን የመረጥኩት ለህዝብ በነጻ ስለተለቀቀ ብቻ ነው። ሌላ የተለ ምክንያት የለኝም።

ግምገማው በሚከተሉት ርእስ ነገሮች ላይ ይሆናል።
Quote:

1. ታሪክ Film Story
2. ገጸባህሪያት፣ Character and characterazation
እድገት፣ Character development
አላማ Character's goal
ተነሳሽነት Mativation
3. ጭውውት Dialog
4. ግጭት Conflict
5. ልብ ሰቀላ Suspense
6. ትልም Plot

ግምገማው የፊልም ስራን ቴክኒካዊ ክፍልን አያካትትም።

ክፍል 1.

1. የፊልሙ ታሪክ ። ሰማያዊ ፈረስ ስለ ምንድን ነው ?

ሰማያዊ ፈረስ ደራሲው አባይን ያናገረበት ወይም ያዳመጠበት ፊልም መሆኑን የሚያመለክት አባይ ነክ ታሪክ አላየሁበትም። ሰማያዊ ፈረስ የተባለው አባይ ወንዝ ከሆነ ርእሱ ከታሪኩ ጋር ግንኙነት የለውም ማለት እደፍራለሁ። ከታሪኩ ጋር የሚስማማ ርእስ ምረጥ ብባል ከዚሁ ፊልም ሳልወጣ ፍሬ ሰላም ለድርሰትዋ የመረጠችውን፣ የናት ጡት ነካሽ፣ የሚለውን አወጣለት ነበር። ምናልባትም የፊልሙ የመጀመሪየ ረእስ ያ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለኝ , የታሪኩ ዋና መስመር የሀገርንና የህዝብን ጥቅም በእፍቅሮተ ነዋይ በመለወጥ ወንጀል ፈጽመው ስልሚያዙ ሰዎች ስለሆነ።

ፊልሙ ሲጀምር በተሾመ የሚመራ አምስት ሰዎች የያዘ አንድ ማፊያ መሰል ቡድን፣ ለውጭ ሰዎች ተቀጥሮ የአቶ እስክንድር አባተን ሳይንሳዊ ጥናት ለመስለብ ሲመካክርና እቅድ ሲያወጣ እናያለን። የሚያልቀው ይሄው ቡድን በህግ ቁጥጥር ስር ሲውል እንጂ የእስክንድር ጥናት ተሰፋ እንደሰጠን አባይ ወንዝን አትንኖ ዝናብ ሲያዘንብ አይደለም።

በእርግጥ ደራሲው የነካካው የኣባይ ጉዳይ በቀላሉ የሚታይ ነገር አይደለም። ከስክሪኑ በስተጀርባ አንድ ትልቅ አሳሳቢና ቁጭት ቀስቃሽ ጥያቄ መለጠፉን ማንም አይስትም። አባይን የሚየክል ስንቱን አብልቶና አተጥቶ ተርፎ ባህር የሚገባ ወንዝ እያለን እንዴት በረሀብ የታወቅን ተመጽዋቾች እንሆናለን የሚለው፣ እስካሁን ምላሽ ያላገኘው፣ የብዙሀን ጥያቄ አለ። ደረሲው ጥያቄውን በተለያየ ምስል አንስቶ አሳይቶናል። መላኩ በቲቪ ስለ አባይ የሚያየው፣ ጴጥሮስም እቤቱ የሰቀለው የፏዋፏዋቴው ስእል፣ በመጨረሻ እስክንድር ራሱ በአካል ሄዶ ጢስ ኣባይን ሲጎበኝ የምናየው እንደ ሰጋር ፈረስ እየተቅበጠበጠ የሚወርደው የውሀ ፏዋፏዋቴ አንዳች የቁጭት ስሜት ይቀሰቅሳል። ፊልሙ በአሁኑ ሰዓት በነጻ ለህዝብ መለቀቁ ምናልባት አሁን ከተከሰተው የረሀብ ችግር ጋር አዛምደን እንድናይ ሊሆን ይችላል።

ሰማያዊ ፈረስ የምርምር ፊልም አይደለም። ስለ ስክንድር ሳይንሰዊው ጥናት ብዙ የሚናገረው ነገር የለም። በኔ እምነት ሰማያዊ ፈረስ የወንጀል ፊልሞች ውስጥ የሚመደብ ፊልም ነው። የስክንድርን አላማ ከግብ ለማድረስ ከሚያሳየው ትይንት ይበልጥ የተወሰኑ ሆዳሞች ራሳቸውን ከሀገር አስቀድመው ለግል ጥቅም ሲሩዋሩዋጡና በመጨረሻም ዘብጢያ ሲወርዱ ነው የሚየሳየው።

ዋናው ገጸ ባህሪ እስክንድር እንድመሆኑ መጠን፣ የታሪኩ ዋና መስመር የሱን አላማ ከግብ ማድረስ ሆኖ በሂደት እነተሾመ እንቅፋት ሲሆኑበት ማሰየት ነበረበት። እንደዚያ ከሆነ ፊልሙ መከተል የነበረበት ሻል ያለ መንገድ አለ። ይኸውም ፊልሙ በሀገራችን በተደጋጋሚ የሚከሰተውን የድርቅ ችግርና በመካያው የሚጠፋውን የኢትዮጵያዊያን ህይወት ከዶክመንታሪ ፊልሞች ቀንጭቦ በማሳይት ቢጅምር፣ በጣም ህይለኛ የሆን የተመልካች ስሜት መቀስቀስ በቻለ ነበር። ወዲያው ስክንድር "ከእንግዲህ አንድ ኢትዮጵያዊ በረሀብ አይሞትም " በማለት ወስኖ ሲነሳ ቢታይ ተመልከች ሁላ በተሰፋና በጉግት እሱን መጥቀበቅ ይጀምር ነበር። ስክንድር አውሮፓን ጥሎ ሀገሩን ከድርቅ ችግር ሊታደጋት ሲመጣ ቦሌ አ ማ ድረስ መጥቶ የተቀበለው ሰው ባይኖርም፣ ፊልም ተመልካቹ ከአይሮፕላን ማረፊያ ሲወጣ በጭብጨባ ይቀበለው ነበር። ከዚያ በሁዋላ ፊልሙ እስክንድርን በዋናነት እያሳየ እስከ አላማው መሳከት ወይም አለመሳካት ድረስ መዝለቅ ነበረበት፣ እንጂ እነ ተሾመ ሲያዙ ማብቃት አልነበረበትም። ፊልሙ ስለ ወንጀል፣ አላማው ወንጀለኞቹን ማስያዝ ከሆነ ግን ርእሱ የናት ጡት ነካሽ ተብሎ ባለው መልክ መቅረቡን መቀበል ይቻላል።

በስክንድር መሪ ተዋኒነት መታየት ስለነበረባቸው ትእይንቶች ወደፊት በትልም፣ በግጭትና በልብ ሰቀላ ርእሶች ስር እጠቃቅሳለሁ።

---

በጣም ደስ የሚል ሂስ ነው ! ይቀጥል :: Cool ፊልም ዋርካ ላይ ሲተች ብዙም አላየሁም ::

አድናቂህ

ብራንነ

———————————

Password በጣም ሀሪፍ ግምገማ ነው :: ባነሳሀቸው ነገሮች እስማማለሁ ::

ደራሲው ውሀውንአትኖ ዝናቡን በማዝነብ እና ከሱጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ትቶ ወደወንጀሉ ባብዛኛው ያተኮረው : ያኛው ብዙ ስራ : ብዙ ማሰብ እንዲሁም more creative መሆንን ስለሚጠይቅ ይመስለኛል :: እናም በቀላሉ ሊወጣው የሚችለውን መረጠ : የፊልሙን ታሪክ አበላሸው ::

እስኪ በነካ እጅህ ስለዚሁ ፊልም ስለሲኒማ ጥበቡ ( cinimathograpy) የሚሰማህን ጨምረህ አጫውተን :: እንደሚታወቀው ጽሁፎ (script) እና ሲኒማ ጥበብ ይለያያሉ :: በ oscar እና በመሳሰሉት እንደምናውቀው የፊልሙ ዳይሪክተር በ ሲኒማ ጥበቡ ሲደነቅ script writer ደግሞ በሌላ catagory ነው የሚታየው :: በሲኒማ ጥበቡ የተደነቀ እና የተሸለመ ፊልም በ script እዚህ ግባ የማይባል ሊሆን ይችላል ::

ሲታ

ክፍል ሁለት።

ገጸ ባህሪያትና እድገታቸው

አንድ የፊልም ታሪክ ሃሳብ ከተወጠነ በሁዋላ ቀጣዩ ስራ ያን ታሪክ ሊሰሩ የሚችሉ ገጸ ባህሪያት መፍጠርና መሳል ነው። ፊልም፣ ተመልካችን በስሜት ወጥሮ እንዲይዝ ታቅዶ የሚሰራ ስለሆነ፣ ስሜት እንዲቀሰቀስ፣ እንዲወጠርና እንዲዘና የሚያደርጉ ተሪኩን የሚሰሩ ገጸ በህሪያትን በሚገባ መሳል ያስፈልጋል። የምንደሰተውም ሆነ የምናዝነው፣ የምንተክዘውም ሆነ የምንስቀው በገጸ ባህሪያቱ በኩል ስለሆነ በተወሰነ ደረጃ ልናውቃቸውም ይገባል።

የምንወዳቸው ገጸባህሪያት አላማ ሲሳካ ደስ ይለናል። ሲከሽፍባቸው ይከፋናል። አደጋ ሲያንዣብብባቸው ስጋት ያድርብናል። ተመልካች እንዲህ የሚሰማው ፊልሙ እውነት ሲመስለው ብቻ ነው። ፈጠራ መሆኑን ቢያውቅም ፊልሙን በሚየይበት ቅጽበት እውነተኛ መስሎ እንዲታየው ከተደረገ የገጸባይሪያቱ ስሜት እየተሰማው ይቀያል። አንድ ፊልም ያን ማድረግ ከቻለ ተዋጥቶለታል ማለት ይቻላል። የተመለካች ስሜት መሳብ ካልቻለ ግን ችግር አለበት ማለት ነው። ከችግሩ አንዱ የገጸባህሪያት አሳሳልና አበለጻጸግ ወይም እድገት በቂ ሳይሆን ሲቀር ነው።

ለገጸ ባህሪያት እድገት ዋናው መሰረት ኮከብ ገጸባህሪው ተጨባጩ አላማው ላይ ለመድረስ

ያለው ተነሳሽነት ነው። ኮክብ ገጸባህሪው ወደ ተጨባጭ አላማው በሚያደርገው ጉዞ የሚገጥመው ውጣ ውረድ ነው የሱንና የሌሎቹ ውላዊ ባህሪ እየተገለጠልን የሚመጣው። ተጨባጩ አላማ ያልኩት ያለምክንየት አይደለም። ሁሌም ውስጣዊ የሆነ ሌላ ስውር ኣላማ ወይም ፍላጎት ስለሚኖር ነው። ያ በገጸ ባህሪው ውስጥ ያለ፣ ለተመልካች የማይታይ፣ ስነልቦናዊ ረሀብን የማስታገስ ፍላጎት ነው።

ለምሳሌ የስክንድር ተጨባጭ ኣላማ ወንዝ አትንኖ ዝናብ ማዝነብ ነው። ስውር ኣላማው ግን ለአስራ አራት ዓመታት ያለመውንና የደከመበትን ጥናት ውጤት በተግባር ሲተረጎም በማየት የሚያገኘው የመንፈስ እረፍትና እርካታ፣ የሳቁበትንና የተሳለቁበትን በማሳየት እልህን መወጣት፣ ከዚያም ከህዝብ ክብርና ሞገስ ማግኘት ነው። ሰው አንድ በጎ ስራ ሲሰራ ከንጹህ ሰብዓዊና ወገናዊ ስሜት በመነሳት ያደረገው እንደሆነ እንጂ የራሱን ግለዊ ስሜት ለማርካትም እንዳደረገው አያምን ይሆናል። ግን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ በግልጽም ሆነ በህቡዕ የግል ጥቅም ጨርሶ የሌለበት በጎ ስራ አለ ማለት የሰቸግራል። በመሰረቱ ያ ስውር አላማ ወይም ውስጣዊ ፍላጎት ነው ገጸባህሪውን እረፍት ነስቶ ለተገባርና ለውጤት የሚገፋፋው። ፊልም ከተጨባጩ ኣላማ አልፎ የስውር ፍላጎትን መሳካትና የውስጣዊ ጥማት መርከትን ሲየሳይ ደረጃው ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ይሆናል።

የገጸባህሪውን ስውር ፍላጎት መሳካት መዳሰስ የሚችል ፊልም ለመስራት ገጸባህሪያት፣ በተለይም ዋና ዋናዎቹ በደንብ መሳል አለባቸው። ተሳለ , ማለት በፊልም ቁዋንቁዋ ተመልካቹ የገጸባህሪውን ጸባይ፣ ዐመል፣ ፍላጎት፣ እንዲሁም ከታሪኩ በፊት ያሳለፈውን ህይወት ከሞላ ጎደል ሲያውቅ፣ ፍርሀቱን ጭንቀቱን፣ እልሁን፣ ፍቅርና ጥላቻውን ሲረዳ፣ ጠንካራና ደካማ ጎኑን ሲገነዘብ ነው።

ገጸባህሪው ከተሳለ በሁዋላ እንድንወደው ወይም እንድንጠላው፣ እንድንጨክንበት ወይም እንድናዝንለት እንዲሁም ውስጠ ምስጢሩን እንድናውቅ ሊያደርጉን የሚችሉት ከእፉ የሚወጡት ቃላትና ሲሰራቸው የምናየው ተግባራት ስለሆኑ የሚናገሩትንና የሚያደርጉት ታሪኩ ሊያስተላልፍ በምንፈልገው ስሜት መሰረት መሆን አለበት። በሰማየዊ ፈረስ ታሪክ ዋናው ገጸባህሪ እስክንድር እባተ ነው። ተመልካቹ የሱ ዓላማ ግቡን ሲመታ ማየት ይፍልጋል። ስለዚህ ተመልካቹ ስክንድርን እንዲወደው፣ ለስክንድር እንዲቀርቀር፣ እንዲጨነቅና እንዲያዝን ማድረግ ያስፈልጋል። ያን ስሜት ከመጀመሪያው መቀስቀስ ይቻልበት የነበረበት ትይንት የቦሌ አ ማ ትይንት ነው።

እስክንድር ከ 14 አመታት በሁዋላ አገሩ ሲገባ የተቀበለው ወዳጅ ዘመድ አልነበረም። እዚህ ላይ ደረሲው አዘኔታ ለመቀስቀስ ጥሩ ምክንያት ተጠቅሞአል። በፊልም ስራ፣ አንድ የሚታዘንለት መሪ ገጸባህሪ መፍጠር ትልቅ ጥበብ ነው። በዘዴ ከተሰራበት ተመልካችን በስሜት መያዝ ያስችላል። ስክንድርን የሚቀበለው ሰው አለመኖሩ ብዙ መግለጽ የሚችል ትይንት ነው። አገሪቱ ባሳለፈችውን መራር የጦርነት፣ የአብዮትና የረሀብ ዘመናት ወዳጅ ዘመዶቹ በሞት ማለቃቸውንና በስደት መጥፋታቸውን ሊጠቁም የሚችል ነበር። ያ መገለጥ የሚችለው በስክንድር ስሜትና ቦሌ አ መ መውጫ ላይ በነበረው ህዝብ ንጽጽር ነበር።

አስረጅ።

ከውጭ የሚመጡት ኢትዮጵያዊያንን ዘመድ ወዳጅ እየተቀበል አቅፎ ሲስማቸው ቢታይ (ትይንቱ ከእስክንድር ግንባር አንጻር ቢታይ ) እና እሱ የሚሳሳምና የሚተቃቀፈውን ህዝብ አታዘበ በትዝታ እንደሄደ፣ አፉ ትንሽ ተከፍቶ፣ አይኑ እንባ ሲያቀር ቢታይ፣ ከዚያም እንባውን እየታገለ፣ ከሻንጣ ተሸካሚዎችና ታክሲ ነጂዎች ጋር መነጋገር እቅቶት ቢታይ የተመልካቹን ልብ ይነካ ነበር ብዬ አምናለሁ።

ያ ስንት መናገር የሚችል አይን እንደ ፓይለት በጥቁር መነጽር ተሸፍኖ፣ እስክንድርም የ 14 ዐመት ናፍቆት እንዳለበት እንግዳ ሳይሆን እንደ ዱባይ ተመላላሽ ምንም ስይደናበርና ግርምታ ሳይታይበት ወጣ። የቦሌው ትይንት ላይ ተመልካቹ ለስክንድር ማድረግ የሚችለው ልዩ ስሜታዊ አቀባበል እምልጦአል።

እንደ ሰማያዊ ፈረስ አይነት ፊልም ላይ ዋናውን ገጸባህሪ ተወዳጅ ማድረግ የግድ ይላል። አልያ ፊልሙ አይሰራም። በገሀዱ አለም ለምንወዳቸው እንደምናስብና እንደምንቀረቀር በፊልምም ገጸባህሪውን ከወደድነው እናስብለታለን፣ እንጨነቅለታለን።

አንድን ገጸ ባህሪ ተመልካች እንዲወደው፣ ደራሲው ምን ማድርግ አለበት ? መልሱ ቀላል ነው። ገጸባህሪው በጎ ስራ ሲስራ ማስይት፣ ለተበደለ ሲቀረቀር፣ ለተገፋ ሲያዝን፣ ለሀቅ ሲዋደቅ። በቃ። እንዲህ አይነት ሰው ተወዳጅ ነው። ቀልደኛና ተጫዋች፣ ደፋርና ብልህ ገጸባህሪም ይወደዳል።

ተመልካች የሰማያዊ ፈረስን መሪ ገጸባህሪ፣ እስክንድር አባተን እንዴት ያየዋል ? ምን ያህል ይወደዋል ? እስክንድር እሚወደድ ሰው ነው ? ምን ያህሉ ተመልካች ነው የሱን አይነት ህይወት፣ ምኞትና አላማ ያለው ? ተመልካች ከራሱ ህይወት ጋር የሚመሳስል ነገር ማየት ይወዳል። ሰማያዊ ፈረስ ውስጥ ከብዙሀኑ ተመለከች ህይወት ጋር የሚመሳሰል ኑሮ ያለው ገጸባህሪ አለን ?

ሰማያዊ ፈረስ ላይ "እስክንድር ከለማኙ ጋር ትይንት " እስክንድርን ተወዳጅ ለማድረግ የተሞከረበት ትይንት ይመስለኛል፣ እስክንድር መመጸወቱና ከለማኙ ጋር መወያየቱ፣ መቃለዱ። ቀልደኛ ሰው ይወደዳልና። ግን ትይንቱ የተፈለገውን ስሜት ሳይሆን ተቃራኒውን ሳይጭር አልቀረም። ስክንድር የያዘውን አይነት መኪና የሚይዙ ግለ ሰቦች በሰፊው ተመልካች ዘንድ ተወዳጅነታቸው ምን ያህል ነው ? ፓጃሮ፣ ፎርዊል መኪና ወዘተ ከሙስናና ከዘረፋ ጋር የሚዛመድ ምስልን ነው የሚሰጠው። መኪናውን ከደሀው ወጣት ጋር ማየትና ማስተየይት፣
የእስክንድር ንግግር / "እንዴት ነው ጤነኛ እጅና እግር እያለህ ልመና " ብሎ ማለቱ፣ "ዝናብ ጠፋ ተሰደድን፣ ማዘርና ብራዘር እኛው፣ " ሲለው ብር ብቻ ሰጥቶት መሄዱ ተወዳጅነት የሚፈጥር ድርጊያ አይደለም።

በዚህ አጋጣሚ ፊልሙ ማሳየት የነበረበት ለእስክንድር ተነሳሽነት መሰርት የሚሆን ትይንት ነበር። እስክንድር ድሀውን ወጣት
/ "ና 'ሲኪ ና እጫውተኝ "/ ብሎ ወጣቱን መኪና ውስጥ አስግብቶ የድርቅንና የረሀብን ችግር ከቀመሰው ወጣት አፍ መስማት ነበረበት። ወጣቱ ታሪኩን ሲያወራ ፊልሙ ቃሉን ተከትሎ

የረሀብን መቅሰፍት የሚያሳይ ከዶክሜንታሪ የተቀነጨበ ትይንት ለተወሰን ደቂቃ ቢያሳየን፣ ቀጥሎ የስክንድር አይን በርበሬ መስሎ እንባ ሲያቀር ቢታይ፣ ተቆርቋሪነቱና ወገን ወዳድነቱ ብቻ ከፍተኛ ተወዳጅነትን ያተርፍለት ነበር።
እስክንድር ሊታደጋቸው የመጣላቸውን ሰዎች፣ የወጣቱ እናትና ወንድምን፣ ፊልሙም አለሳየን፣ ዋና ገጸባህሪም ሊያየቸው አልተጨነቀም። ስለዚህ ተመልከቹ እስክንድርን መኪና ቢገጨው ባይገጨው፣ ተሾመ ቢገድለው ባይገድለው ስሜት አይሰጠውም። አይወደውማ። ስክንድር ያለው ተወዳጅነት ካለ ከወካዩ ተዋኒ ከሰረዊት ፍቅሬ ቁመናና መልከቀናንት፣ ፈገግታና አነጋገር ያገኘው ነው።

ይቀጥላል።

ፓስወርድ .

——————————

ሲታ !!! እንደጻፈ(ች)ው:
Password በጣም ሀሪፍ ግምገማ ነው :: ባነሳሀቸው ነገሮች እስማማለሁ ::

ደራሲው ውሀውንእትኖ ዝናቡን በማዝነብ እና ከሱጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ትቶ ወደወንጀሉ ባብዛኛው ያተኮረው : ያኛው ብዙ ስራ : ብዙ ማሰብ እንዲሁም more creative መሆንን ስለሚጠይቅ ይመስለኛል :: እናም በቀላሉ ሊወጣው የሚችለውን መረጠ : የፊልሙን ታሪክ አበላሸው ::

እስኪ በነካ እጅህ ሰለዚሁ ፊልም ስለሲኒማ ጥበቡ ( cinimathograpy) የሚሰማህን ጨምረህ አጫውተን :: እንደሚታወቀው ጽሁፎ (script) እና ሲኒማ ጥበብ ይለያያሉ :: በ oscar እና በመሳሰሉት እንደምናውቀው የፊልሙ ዳይሪክተር በ ሲኒማ ጥበቡ ሲደነቅ script writer ደግሞ በሌላ catagory ነው የሚታየው :: በሲኒማ ጥበቡ የተደነቀ እና የተሸለመ ፊልም በ script እዚህ ግባ የማይባል ሊሆን ይችላል ::

ሲታ

ሲታ
ለ 'አስተያየትህ አመሰግናለሁ .

ከመግቢያው ላይ እንደገለጽኩት ግምገማው ቴክኒካል ክፍሉን አይዳስስም ብዬ ነበር። የምገመግመው ከተውኔቱ ጽሁፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ርእሰነገሮች እንጂ cinematographyን በተመለከተ ጠለቅ ያል እውቀት ስለሌለኝ ብዙ ማለት ያስቸግረኛል። የፊልም ስራ ባለብዙ ዘርፍ ጥበብ ስለሆነ ለየዘርፉ ባለሙያው ሲተችበት ይሻላል። አልያ መቀባጠር ነው የሚሆነው።

ደራሲው ወደ ወንጀሉ ያተኮረው፣ ያኛው ብዙ ማሰብ ስለሚጠይቅ ይሆናል ስላልከው ጉዳይ፣

ችግሩ ያ አይመስለኝም። ውሀ እንደተነነ ማስመሰልና ዝናብ ማስዘነብ ማሳየት የሮኬት ሳይቲስት መሆን አይጠይቅም። ያን በፊልም ማሳየት ካልቻልክ ጭራሹን ፊልም የሚባል ነገር መሞከር አልነበረብህም። ሳይንሱ፣ ማለትም የሶላር ኢነርጂን በመጠቀም ውሀ መንፍላትና ያን እንፋሎት ከተወሰነ ቦታ ሄዶ እንዲዝንብ ማድረግ መቻሉን ተመልካቹ እንዲያምን ስራዊት የተጠቀመው ጥሩ ዘዴ አለ። ፊልሙ ሲጀምር፣ የወንጀለኞቹ መሪ , ተሾመ , በኢኒመሺን ፊልም እየታገዘ ለቡድኑ ያብራራውን እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ያ foreshadowing ማለትም ቅድመ ጥቆማ መሆኑ ነው። ግን በቂ አልነበረም። በተጨማሪም እነ ተሾመ ከዶለሩ እንጂ ከዝናቡ ጉዳይ ስሌለላቸው ሳይንሱን የማብራራቱ ነገር በነሱ አያምርም። ያን ማብራራት የነበረበት ስክንድር ራሱ ነው። በኢኒመሺን ፊልም ከማስርዳት፣ ተኣመኒነት ለማጠንከር በላቦራቶር ወስጥ ቁንጽል ሚኒ ኤክስፔርመንት ማሳየት ይመርጡዋል።

ለምሳሌ ያህል 'BACK TO THE FUTURE. የተሰኘውን ግሩም ፊልም እንውሰድ። ያን crazy scientist ታስተውሳልህ። Martyን ከ 1935 back to the future፣ ወደ 1985 ለመላክ የሚያስችለውን ቴክኒክ ላብ ውስጥ በመጫወቻ እቃዎች ነው የሚያሳየን። ያ experiment ሁለት አላማ አለው። አንዱ ከዚያ ቴክኖሎጂ ካልዳበረበት ዘመን በጊዜ ጉዙ ማድረግ የመቻሉ ነገር አጠራጣሪ ስለሆነ ማስተማመኛ እንዲሆን ቅድመ ጥቆማ foreshadowing, ሲሆን ሁለተኛውና ዋናው ያን የተራቀቀ ውስብስብ ሳይንስ አንድ ተመልካች ሊረዳው በሚችል መጠን ቁመቱን፣ ክብደቱን፣ ፍጥነቱንና ውስጠ ፍጥረቱን ማሳነስ ነው። በትንሹ ሲሆን ሲለሚገባን።

ደራሲ ስራዊት ፍቅሬ ወደ ወንጀሉ ያመዘነበት አንዱ ምክንያት በመጀመሪያ ታሪኩ ስለምን እንደሆነ ለይቶ ያወጣው የታሪክ መስመር ካለመኖሩ ይመስለኛል። ስማያዊ ፈረስ፣ የአባይን ወንዝ በማትነን አገሩን ለማልማት ስለሚፍልግ ምሁር ነው የሚል የነጠረ መስመር አልያዘም። መስመር ስላልያዝ ታሪኩ ወደ ወንጀሉ ተንጋደደበት ነው የምለው።

ሁለተኛው ምክንያት ከዋናው ገጸባህሪ ግብ ጋር የተያየዘ ነው ? የአንድ ገጸ ባህሪ ግብ ግልጽ ካልሆነ ታሪኩ እንደ አባይ ወንዝ ራሱ በቀደደው ቦይ ነው የሚፈስው። ከእንዲህ ኣይነት አቅጣጫ -አሳች ችግር ራስን ለመጠበቅ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ጥሩ መልስ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

፩ የዋናው ገጸ በህሪ ዋና ግብ ምንድን ነው ?
መልሱ የወንዝ ውሀ እትንኖ ዝናብ ማዝነብ።

፪ ለምን ዝናብ ማዝነብ አስፈለገው ?
መልሱ በድርቅ ምክንያት የሚጎዳውን ህዝብ ለመታደግ

፫ ገጻባህሪው ባይሳካለት ምን ይፈጠራል ? ማን ይጎዳል ? ማን ይሞታል ? ይህ ነው ዋናው

ጥያቄ what is at stake? if there is nothing at stake , no body cares about the project or the character.

ስማያዊ ፈረስ እነዚህን ጥየቄዎች ለመመለስ ካለመሞከሩ ላይ ይመስለኛል፣ ችግሩ። ገጸባህሪውን የሚያንሳሳው motivation ጉዳይ በደንብ አለመዳበሩ።

——————————————

ሚላግሮ እንደጻፈ(ች)ው:
ግምገማህን እየተከታተልኩት ነው ተደስቼበታለው
በርታ እኔም ብዙ ነገሮችን ለማወቅ እየረደሁኝ ነው ያሉት
እንዲህ ጊዜህን መስዋት አድርገህ ለጥበብ መጨነቅህ ለራሱ
ምን ያህል የጥበብ ሰው እንደሁንክ ያስረዳል ::
በርታ ወዳጄ ብዙ አይኖች እየጠበቁህ ነው ::

ሚላግሮ

ለአስተያየትህ አመሰግናለሁ።

ግምገማውን በተመለከተ ብዙም አስተያዬትና መልስ ስላላይሁ፣ ያንተን ሳይ ለፊልም ጥበብ ልዩ ዝንበሌ ያለህ መሰለኝ፣ ካልተሳሳትኩ።
እናም ካነሳነው ርእስ ሌላም ፊልምና ጥበቡን በተመለከት , (በተለይ screenplay,) ከኔ ገር ለመወያይት ወደ ሁዋላ አትበል።

ክፍል 2
ካለፈው የቀጠለ
ገጸባህሪያትና አደረጃጀታቸው።

ስክንድር ተወዳጅ ባህሪ አይደለም ብያለሁ፣

እሱ ተወደጅ ካልሆነ ፊልሙን ተወዳጅ ማድረግ እጅግ ከባድ ነው። የሰማያዊ ፈረስ አይነት በዋናውን ገጸባህሪ ህይወት ዙሪያ የሚጠነጠን ታሪክ ገጸባህሪው በተመልካች ውስጥ የሚያሳድረው ስሜት ወሳኝ ነው። ተመልካች እሱን የሚመስል፣ እንደሱ የሚያስብ፣ እንደሱ የሚመኝ፣ እንደሱ የሚፈራ፣ እንደሱ የሚጫወት ባጠቃላይ እንደሱ ወይም እሱ በቅርብ እንደሚያውቃቸው ሰዎች የሚኖር ሰው ጋር በቀለሉ ራሱን ያመሳስላል። ከምግብ ስጋን ከመጠጥ ሽቫስን የሚጠላ የለም , ግን ወገኑን ከረሀብ ችግር ሊታደግ የመጣ ጀግና ገና ግቡን ሳይመታ በውስኪ የሚጥለቀለቅ ከሆነ የተመልከቹን ልብ ማግኘት ቀላል ይሆንለታል ብዬ አልገምትም።

ተመልካች ለገጸበህሪው እንዲሳሳ ማድረግ በፊልም ተውኔት ውስጥ በጣም የተለመደ ዘዴ ነው። በተሳካ ሁኔታ ከተቀናበረ ተመልካችን የመያዝ ከፍተኛ ሀይል እንደ አለው ይታመንበታል። ይህን ማድረግ የሚቻለው ገጸ ባህሪውን በአሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ እንዲያልፍ በማድረግ ነው፣ ያለፈ ህይወቱን ወይም አሁን የሚገኝበት ሁነታ ተመልካቹን ልብ በሚነካ መልኩ በማሳየት።

ምሳሌ First Blood ላይ John Rambo የተመልካቹን ልብ "audience sympathy" ያገኘው በዚህ መልክ ነው። ፊልሙ የሚጀምረው እሱ ጉዋደኞውን ፍለጋ መጥቶ፣ የጉዋደኛው እናት አለም እንደ ዱሮ፣ እንደ ደጉ ዘመን እንደልሆነች፣ ጉዋደኞቹንም ሰማያዊ ጅብ እንደበላቸው ነግረውት ሲመለስ ነው። ያዝናል። ያሳዝናል።

የሀዘንና የብቸኝነት ስሜት ነው ከራምቦ እንድንወግን የሚያደርገን።

እስክንድር ከውጭ እንደመጣ እምስት ኮከብ ሆቴል ከሚገባ አደገበት ሰፈር ሄዶ፣ ያ ዱሮ ኮራ ብሎ ይታይ የነበረ ቤታቸው ሽረሪት እድርቶበት፣ ደራ ብሎ ይሞቅ የነበረ ግቢያቸው ፈርሶ፣ ሳር ቅጠሉ ያውቀው የነበረ እስክንድር አሁን አንድ የሚያውቀው ሰው ማጠቱ፣ ድሮ የሚየውቀው ሰፈር ወድሞ፣ ሰው ተራቁቶ ቢያገኝ፣ አብሮ አደጎቹን ፍልጋ ጎራ ብሎ አንዱንም ሲያጣ፣

የእናቱን፣ ጉዋደኛ እመት ጤንፍየለሽን አግኝቶ ስላሉትና ስለሌሉት ሲነግሩት፣ በመጨረሻ አዝኖ ሲመለስ ማሰየት ልዩ በጀት የሚጠይቅ አይመስለኝም። የተመልካችን ስሜት መያዝ እንደሚችል ግን አያጠራጥርም።

ሁለተኛዋ ዋና ገጸባህሪ ፍሬሰላም ነች። እስዋስ በተመልከቹ ውስጥ የምታሳድረው ስሜት ምን አይነት ነው ? የምትወደድ ወይስ የምትጠላ ነች ? ባህሪዋ፣ አስተዳደግዋ፣ ስራዋ፣ ቤተሰቦችዋ፣ ጉዋደኞችዋ ለተመልከች የሚታወቁበት ትይንት ታይቶአል ?

በኔ አመለካከት ፍሬሰላም ከሌሎቹ ገ / ባህሪያት በተሻለ ሁኔታ ተቀርጻለች። ደራሲ ነች። በስነጽሁፍ ተመርቃለች። ቀደም ሲል በጻፈችው መጽሀፍ ምክንያት ታስራ ነበር። ከርቸሌን ታውቀዋለች፣ የምትፈራው አትመስልም። ድርሰቶቼን እንባቢ አልተረዳልኝም ብላ ትበሳጨለች። ከአንድ እህትዋ በቀር ሌላ የቅርብ ዘመድ የላትም። እህትዋ የህክምና ባለሙያ ናት። ፍሬሰላም እህትዋን ተጠግታ ነው የምትኖረው።

ፍሬሰላም እነተሾም በወጠኑት ባለቡዙው ሚሊዮን ብር ወንጀል ውስጥ እንድትሳተፍ ሊያደርጉዋት የሚችሉ ሁኔታዎች አሉ። አንዱ በደራሲነት ሙያዋ ሰርታ ራስዋን ማስተዳደር አለመቻልዋ ሊሆን ይችላል። ሌሎች ደረሲያን እንደሚያድርጉት ሌላ ስራ መስራት ያልቻለችበት ምክንየት ግልጽ ባይሆንም፣ የነተሾመ ሴራ ከተሳካ እስክ ስድስት ሚሊዮን ብር የምታገኝበትን ተልእኮ ስለሆነ ለመሳተፍ አላቅማማችም። ግን ለገንዘብ ስትንገበገብ ወይም ለሀብት ስትቁዋምጥ አለመታየትዋ ከሌሎቹ ለየት ያለች መሆንዋን ያስገነዝባል።

ከስክንድር ጋር ከተዋውቅች በሁዋላ ፍቅር እያሸነፋት ስትሄድ እናያለን። ስለ ወንዝ ማትነንና ዝናብ ማዝነብ ፕሮጅክቱ ከስክንድር አፍ ስትሰማ ደግሞ የሀገር ጥቅም ተቀዳሚነትን ስትገነዝብ ትስተዋላለች። የባህሪ ለውጥ እናይባታለን፣ ወላዋይነት ሳይሆን ማደግዋንና

መለወጧን። ሚሊዮን ብር መጀመሪያ ያታልላል፣ ቆየት ሲሉ ግን ከሚሊዮን የሚበልጡ ብዙ ነገሮች እንዳሉ ነው፣ በፍሬሰላም በኩል የምናየው።

ሌሎቹን ባህሪያት በተመለከተ ብዙ የሚባል ነገር ይኖራል። እዚህ ላይ ግን ዳበስ አድርጌ ብቻ ነው የማልፈው። ያ ማለት ተራቸው አነስተኛ ነው ማለት አይደለም። ታሪኩን ወደፊት ለማራመድና የተመልካችን ስሜት ለመያዝ የሁሉም በገጸባህሪያት ተራና አላማ በተቻል ግልጽ አድርጎ ማሳየት ጠቃሚ ነው። ሰማያዊ ፈረስ ያለነ ተሾመ ሊቆም አይችልም። ስለሆነም በደንብ መሳል አለባቸው።

የነተሾም ቡድን አባላት አኑዋኑርና ባህርየት በጣም ከመመሳሰሉ የተንሳ እንዱን ከሌላው በመልክ በቀር በሌላ መስፈርት መለየት ያስቸግራል። አንዱ ችኩል ሌላው እርጎ፣ አንዱ ጨካኝ ሌላው ርህሩህ ቢሆኑ ኖሮ ባህሪየቱ ጎልተው ይወጡ በነበርና በተለዩ። እነዚህ ግን እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ሚስቶቻቸው፣ ቤቶቻቸው፣ መኪኖቻቸው ጭምር ይመሳሰላሉ። አያሳምንም።

ለምን ?

ሌባ ሲባል ሁሉ ጨካኝ አይደለማ። ሌባ ሁሉም ደፋር አይደለማ። ሌቦች ሁሌ በሁሉም ነገር አይስመሙማ። እነሱም በውስጣቸው ቅረኔ አለባቸው። በመሀላቸው አለመተማመንም ይኖራል። ያ ወጥቶ ሲታይ ባህሪያቱ ውን ብቻ ሳይሆኑ በተመልካች ትዝታ ውስጥ ለረጅም ጊዜ መቆየትም ይችላሉ።

አርማጌደን የሚባለው ፊልም ውስጥ ከዊልስ ብሩስ ጋር የሚሰሩትን ነዳጅ አውጪዎች ያስታውሱዋል። አንዱ ከሌላው የሚለይበት ባህሪ በጥንቃቄ ተነድፎ እንደተዘጋጀ ያስታውቃል። ተመሳሳይ ገጸ ባህሪ አይታዩበትም። አንዱ ቀልደኛ ሌላው ቁምነገረኛ፣ አንዱ ፈሪ ሌለው ደፋር፣ ወዘተ ናቸው። ገጸ ባህሪያት ተመሳሳይ ከሆኑ፣ ለታሪኩም ለበጀቱ ሲባል አንዱን ማስወጣት ይሻሻል። አለበለዚያ ለሁሉም የተለየየ የጀርባ ታሪክ፣ አስትደድግና የህይወት አላማ በመስጠት የተለየዩ ባህሪያት እንዲሆኑ ማድርግ። ያኔ ነው ሲስማሙ ብቻ ሳይሆን ሲጨቃጨቁም ማየት የምንችለው። ብሎም እውነታን በማንጸባረቅ ተመልከች መማረክ ----

---

ክፍል 2
ካለፈው የቀጠለ
ገጸባህሪያትና አደረጃጀታቸው።

ስክንድር ተወዳጅ ባህሪ አይደለም ብያለሁ፣

እሱ ተወደጅ ካልሆነ ፊልሙን ተወዳጅ ማድረግ እጅግ ከባድ ነው። የሰማያዊ ፈረስ አይነት በዋናውን ገጸባህሪ ህይወት ዙሪያ የሚጠነጠን ታሪክ ገጸባህሪው በተመልካች ውስጥ የሚያሳድረው ስሜት ወሳኝ ነው። ተመልካች እሱን የሚመስል፣ እንደሱ የሚያስብ፣ እንደሱ

የሚመኝ፣ እንደሱ የሚፈራ፣ እንደሱ የሚጫወት ባጠቃላይ እንደሱ ወይም እሱ በቅርብ እንደሚያውቃቸው ሰዎች የሚኖር ሰው ጋር በቀለሉ ራሱን ያመሳስላል። ከምግብ ስጋን ከመጠጥ ሽሻሽን የሚጠላ የለም , ግን ወገኑን ከረሀብ ችግር ሊታደግ የመጣ ጀግና ገና ግቡን ሳይመታ በውስኪ የሚጥለቀለቅ ከሆነ የተመልከቹን ልብ ማግኘት ቀላል ይሆንለታል ብዬ አልገምትም።

ተመልካች ለገጸበህሪው እንዲሳሳ ማድረግ በፊልም ተውኔት ውስጥ በጣም የተለመደ ዘዴ ነው። በተሳካ ሁኔታ ከተቀናበረ ተመልካችን የመያዝ ከፍተኛ ሀይል እንደ አለው ይታመንበታል። ይህን ማድረግ የሚቻለው ገጸ ባህሪውን በአሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ እንዲያልፍ በማድረግ ነው፣ ያለፈ ህይወቱን ወይም አሁን የሚገኝበት ሁነታ ተመልካቹን ልብ በሚነካ መልኩ በማሳየት።
ምሳሌ First Blood ላይ John Rambo የተመልካቹን ልብ "audience sympathy" ያገኘው በዚህ መልክ ነው። ፊልሙ የሚጀምረው እሱ ጉዋደኛውን ፍለጋ መጥቶ፣ የጉዋደኛው እናት አለም እንደ ዱሮ፣ እንደ ደጉ ዘመን እንደልሆነች፣ ጉዋደኞቹንም ሰማያዊ ጅብ እንደበላቸው ነግረውት ሲመለስ ነው። ያዝናል። ያሳዝናል።
የሀዘንና የብቸኝነት ስሜት ነው ከራምቦ እንድንወግን የሚያደርገን።

እስክንድር ከውጭ እንደመጣ አምስት ኮከብ ሆቴል ከሚገባ አደገበት ሰፈር ሄዶ፣ ያ ዱሮ ኮራ ብሎ ይታይ የነበረ ቤታቸው ሽረሪት አድርቶበት፣ ደራ ብሎ ይሞቅ የነበረ ግቢያቸው ፈርሶ፣ ሳር ቅጠሉ ያውቀው የነበረ እስክንድር አሁን አንድ የሚያውቀው ሰው ማጠቱ፣ ድሮ የሚየውቀው ሰፈር ወድሞ፣ ሰው ተራቁቶ ቢያገኝ፣ አብሮ አደጎቹን ፍልጋ ጎራ ብሎ አንዱንም ሲያጣ፣
የእናቱን፣ ጉዋደኛ እመት ጤንፍየለሽን አግኝቶ ሰላሉትና ስለሌሉት ሲነግሩት፣ በመጨረሻ አዝኖ ሲመለስ ማሰየት ልዩ በጀት የሚጠይቅ አይመስለኝም። የተመልካችን ስሜት መያዝ እንደሚችል ግን አያጠራጥርም።

ሁለተኛዋ ዋና ገጸባህሪ ፍሬሰላም ነች። እሰዋስ በተመልከቹ ውስጥ የምታሳድረው ስሜት ምን አይነት ነው ? የምትወደድ ወይስ የምትጠላ ነች ? ባህሪዋ፣ አስተዳደግዋ፣ ስራዋ፣ ቤተሰቦችዋ፣ ጉዋደኞችዋ ለተመልከች የሚታወቁበት ትይንት ታይቶአል ?

በኔ አመለካከት ፍሬሰላም ከሌሎቹ ገ / ባህሪያት በተሻለ ሁኔታ ተቀርጻለች። ደራሲ ነች። በስነጽሁፍ ተመርቃለች። ቀደም ሲል በጻፈችው መጽሀፍ ምክንያት ታስራ ነበር። ከርቸሌን ታውቀዋለች፣ የምትፈራው አትመስልም። ድርሰቶቼን እንገባቢ አልተረዳልኝም ብላ ትበሳጫለች። ከአንድ እህትዋ በቀር ሌላ የቅርብ ዘመድ የላትም። እህትዋ የህክምና ባለሙያ ናት። ፍሬሰላም እህትዋን ተጠግታ ነው የምትኖረው።

ፍሬሰላም እነተሾም በወጠኑት ባለቡዙው ሚሊዮን ብር ወንጀል ውስጥ እንድትሳተፍ ሊያደርጉዋት የሚችሉ ሁኔታዎች አሉ። እንዱ በደራሲነት ሙያዋ ሰርታ ራስዋን ማስተዳደር አለመቻልዋ ሊሆን ይችላል። ሌሎች ደረሲያን እንደሚያድርጉት ሌላ ስራ መስራት ያልቻለችበት ምክንየት ግልጽ ባይሆንም፣ የነተሾመ ሴራ ከተሳካ እስክ ስድስት ሚሊዮን ብር

የምታገኝበትን ተልእኮ ስለሆነ ለመሳተፍ አላቅማማችም። ግን ለገንዘብ ስትንገበገብ ወይም ለሀብት ስትቁዋምጥ አለመታየትዋ ከሌሎቹ ለየት ያለች መሆንዋን ያስገነዝባል።

ከስክንድር ጋር ከተዋውቅች በሁዋላ ፍቅር እያሸነፋት ስትሄድ እናያለን። ስለ ወንዝ ማትነንና ዝናብ ማዝነብ ፕሮጅክቱ ከስክንድር አፍ ስትሰማ ደግሞ የሀገር ጥቅም ተቀዳሚነትን ስትገነዝብ ትስተዋላለች። የባህሪ ለውጥ እናይባታለን፣ ወላዋይነት ሳይሆን ማደግዋንና መለወጧን። ሚሊዮን ብር መጀመሪያ ያታልላል፣ ቆየት ሲሉ ግን ከሚሊዮን የሚበልጡ ብዙ ነገሮች እንዳሉ ነው፣ በፍሬሰላም በኩል የምናየው።

ሌሎቹን ባህሪያት በተመለከተ ብዙ የሚባል ነገር ይኖራል። እዚህ ላይ ግን ዳበስ አድርጌ ብቻ ነው የማልፈው። ያ ማለት ተራቸው አነስተኛ ነው ማለት አይደለም። ታሪኩን ወደፊት ለማራመድና የተመልካችን ስሜት ለመያዝ የሁሉም በገጸባህሪያት ተራና አላማ በተቻል ግልጽ አድርጎ ማሳየት ጠቃሚ ነው። ሰማያዊ ፈረስ ያለነ ተሾመ ሊቆም አይችልም። ስለሆነም በደንብ መሳል አለባቸው።

የነተሾም ቡድን አባላት አኑዋኑርና ባህርየት በጣም ከመመሳሰሉ የተንሳ እንዱን ከሌላው በመልክ በቀር በሌላ መስፈርት መለየት ያስቸግራል። አንዱ ችኩል ሌላው እርጎ፣ አንዱ ጨካኝ ሌላው ርህሩህ ቢሆኑ ኖሮ ባህሪየቱ ጎልተው ይወጡ በነበርና በተለዩ። እነዚህ ግን እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ሚስቶቻቸው፣ ቤቶቻቸው፣ መኪኖቻቸው ጭምር ይመሳሰላሉ። አያሳምንም።

ለምን ?

ሌባ ሲባል ሁሉ ጨካኝ አይደለማ። ሌባ ሁሉም ደፋር አይደለማ። ሌቦች ሁሌ በሁሉም ነገር አይስመሙማ። እነሱም በውስጣቸው ቅረኔ አለባቸው። በመሀላቸው አለመተማመንም ይኖራል። ያ ወጥቶ ሲታይ ባህሪያቱ ውን ብቻ ሳይሆኑ በተመልካች ትዝታ ውስጥ ለረጅም ጊዜ መቆየትም ይችላሉ።

አርማጌዶን የሚባለው ፊልም ውስጥ ከዊልስ ብሩስ ጋር የሚሰሩትን ነዳጅ አውጬዎች ያስታውሱዋል። አንዱ ከሌላው የሚለይበት ባህሪ በጥንቃቄ ተነድፎ እንደተዘጋጀ ያስታውቃል። ተመሳሳይ ገጸ ባህሪ አይታዩበትም። አንዱ ቀልደኛ ሌላው ቁምነገረኛ፣ አንዱ ፈሪ ሌለው ደፋር፣ ወዘተ ናቸው። ገጸ ባህሪያት ተመሳሳይ ከሆኑ፣ ለታሪኩም ለበጀቱ ሲባል አንዱን ማስወጣት ይሻሻል። አለበለዚያ ለሁሉም የተለየየ የጀርባ ታሪክ፣ አስትደድግና የህይወት አላማ በመስጠት የተለየዩ ባህሪያት እንዲሆኑ ማድርግ። ያኔ ነው ሲስማሙ ብቻ ሳይሆን ሲጨቃጨቁም ማየት የምንችለው። ብሎም እውነታን በማንጸባረቅ ተመልከች መማረክ ----

---

ወዳጄ ፓስወርድ ግምገማህን ወደድኩት መውደድ ብቻ አይደለም መሳተፍም ሞከርኩ ::
በመጀመሪያ ታሪኩ ላይ ያስቀመጥካቸውን አንዳንድ አስተያየቶች በተመለከተ ጥቂት ልበል
......
የፊልሙ ታሪክ ........."ሰማያዊ ፈረስ ስለ ምንድን ነው ?""

ብለህል ስለምን እንደሆነ ጠፍቶህ አይደለም ::ገብቶህ ብዙ ብለህል ለዚህም አድንቄሀለሁ ::
ግን "....ሰማያዊ ፈረስ ደራሲ.ው አባይን ያናገረበት ወይም ያዳመጠበት ፊልም መሆኑን
የሚያመለክት አባይ ነክ ታሪክ አላየሁበትም። ...."እንዴት ? አባይን ለማዝነብ ነው አላማው
::የውጭ ሰዎችንም ሰቦ ቅጥረኛ እንዲገዙ ያረገው ይሄው ነው ::ቅጥረኛ ገዢዎቹ ማን
እንደሆኑ ያልተጠቀሰው በጥርጣሬ ሀሳብ ተማልካችን ሰቅዞ ለመያዝ ነው ::ማን ይሆን
ግብጾች ?ወይስ ሌላ ፈጠራውን ፈላጊዎች ? እርግጥ ፍንጭ ይሰጣል ::ተጨማሪ
"....ሰማያዊ ፈረስ የተባለው አባይ ወንዝ ከሆነ ርእሱ ከታሪኩ ጋር ግንኙነት የለውም ማለት
እደፍራለሁ። ..."ብለህል ይህ የራስህ ሀሳብ ነው በደራሲ.ው ዘንድ ወሀውን አትንኖ ሰማይ ላይ
ከወጣ በሁዋላ ነው የሚዘንበው የኢንጂነር እስክንድር ግኝትም ወሀውን አትንኖ ሳማይ
ማውጣት ነው ::የሌሎችን ትኩረት የሳበውም ይሄው ነው ::የታሪኩ አንኩዋር ጨብጥም
ይሄው ነው ::ስለዚህ ""..........ከታሪኩ ጋር የሚስማማ ርእስ ምረጥ ብባል ከዚሁ ፊልም
ሳልወጣ ፍሬ ሰላም ለድርሰትዋ የመረጠችውን፣ የናት ጡት ነካሽ፣ የሚለውን አወጣለት ነበር።
....." ብለህል ::በመጀመሪያ ላልወለዱት ልጅ ስም ማውጣት ወይም ለሰው ፈጠራ ርዕስ
ማውጣት አይሆንም አይታሰብም :: ሌላው የገረመኝ ""....የታሪኩ ዋና መስመር የሀገርንና
የሀዝብን ጥቅም በአፍቅሮተ ነዋይ በመለወጥ ወንጀል ፈጽመው ስልሚያዙ ሰዎች ስለሆነ።
......"ከላይ እንደገለጽኩት ታይቶ የማይታወቀውን ወንዝን አትንኖ የማዝነቢያ ሲ.ስተም /
ፈጠራ /ነው ያ -ያጉዋጉዋቸው ናቸው ጥናቱን ለማግኘት የሚሩዋሩዋጡት ይህ ፈጠራ
ባይስባቸው ዞር ብለው ባላዩት ሌላው ብዙ ትኩረት የሰጠው አባይ ላይ መሆኑ ነው እዛው ድረስ
ሄዶ ማጥናት ያስፈለገው ለረጅም ጊዜ የተመራመረበትን ንድፍ ይዞ ሀገሩ የመጣው ያለበት
ሀገር ወንዝ ጠፍቶ አይመስለኝም ::ደራሲ.ው ታሪኩን በአባይ ላይ ለማረግ ነው ::ስለዚ.ህ
የታሪኩ ምሶሶ አባይ ነው ::

ወዳጄ ፓስወርድ ""...ፊልሙ ሲጀምር በተሸመ የሚመራ አምስት ሰዎች የያዘ አንድ ማፊያ
መሰል ቡድን፣ ለውጭ ሰዎች ተቀጥሮ የእቶ እስክንድር አባተን ሳይንሳዊ ጥናት ለመስለብ
ሲ.መካከርና እቅድ ሲ.ያወጣ እናያለን። የሚያልቀው ይሄው ቡድን በህግ ቁጥጥር ስር ሲ.ውል
እንጂ የእስክንድር ጥናት ተሰፋ እንደሰጠን አባይ ወንዝን አትንኖ ዝናብ ሲ.ያዘንብ
አይደለም። ...."ብለህል እንደህሳብ ስናየው ልክ ሊ.መስል ይችላል ::እጨራረሱን እንደህንድ
ፊልም ያረገውና ተረት ...ተረት ይሆን ነበር ::ከቀማኞች መትረፋን ካሳየህ ቀጣዩ የተመልካች
ግምት መሆን አለበት ::ለተመልካቹ የሆነ የቤት ስራ ካልተወ ምኑ ነው ትውስታው ?ለምሳሌ
በዕኔ ግምት ቀማኛ ከሌለ እንቅፋት ከሌለ ተግባር ላይ ይውላል እላለሁ ::አንተ ደግሞ ሌሎች
ቀማኞች ቢ.ነሱበትስ ትላለህ .......ይሄ ነ የቤት ስራው ::

በአባይ ጉዳይ አይደለም ጭብጡ የእናት ጡት ነካሽ በሆኑ ዙሪያ ነው ለሚለው ሀሳብህ ራስህ
ወረድ ብለህ የጻፍከው መልስ ይሆናል እንየው ".....በእርግጥ ደራሲ.ው የነካካው የኣባይ
ጉዳይ በቀላሉ የሚ.ታይ ነገር አይደለም። ከስክሪኑ በስተጀርባ አንድ ትልቅ አሳሳቢ.ና ቁጭት
ቀስቃሽ ጥያቄ መለጠፋን ማንም አይስትም። አባይን የሚየክል ስንቱን አብልቶና አተጥቶ
ተርፎ ባህር የሚገባ ወንዝ እያለን እንዴት በረሀብ የታወቅን ተመጽዋቾች እንሆናለን
የሚ.ለው፣ እስካሁን ምላሽ ያላገኘው፣ የብዙሀን ጥያቄ አለ። ደረሲ.ው ጥያቄውን በተለያየ
ምስል አንስቶ አሳይቶናል። መላኩ በቲቪ. ስለ አባይ የሚያየው፣ ጴጥሮስም እቤቱ የሰቀለው
የፋዋፋዋቴው ስእል፣ በመጨረሻ እስክንድር ራሱ በአካል ሄዶ ጢ.ስ ኣባይን ሲ.ጎበኝ የምናየው
እንደ ሰጋር ፈረስ እየተቅበጠበጠ የሚ.ወርደው የውሀ ፋዋፋዋቴ አንዳች የቁጭት ስሜት
ይቀሰቅሳል። ...." ከዚ.ህ በላይ ምን ማስረጃ አለ ?ገበሬው ተፈናቅሎ ለልመና ወቶ ""አንድ
ብር ላይ ያለው ወንድሜ ናፈቀኝ ...........ሰማይ ገጌ ምድር ፈቄ አለብንና ....እዛው ጎጃም

ሄዶ ባይሆን እንኩዋን ትኩረት አልሳበም ይባላል አባይ አጠገብ ገበሬው ሲለምን ያሳየው ቁጭትን መጫር ብቻ ሳይሆን እንዲነገር ያረገዋል ::
አቀጥላለሁ

——————————————

ባሻ አንደጻፈው
Quote:
ወዳጄ ፓስወርድ ግምገማህን ወደድኩት መውደድ ብቻ አይደለም መሳተፍም ሞከርኩ ::

ግምግማዬን ስለወደድከው በጣም አመሰግናለሁ። በተሳትፎህም ደስተኛ ነኝ። የሚያነብህ ሰው መኖሩን ማወቅ ራሱ ያስደስታል።

Quote:
."ሰማያዊ ፈረስ ስለ ምንድን ነው ?""
ብለህል ስለምን እንደሆነ ጠፍቶህ አይደለም ::ገብቶህ ብዙ ብለህል ለዚህም አድንቄሀለሁ

ይህ ለትችቴ መንደርደሪ እንዲሆን ያስቀመጥኩት እንጂ ማብራሪያ ፈልጌ ያቀረብኩት ጥያቄ አይደለም።

Quote:
ወዳጄ ፓስወርድ ""...ፊልሙ ሲጀምር በተሾመ የሚመራ አምስት ሰዎች የያዘ አንድ ማፊያ መሰል ቡድን፣ ለውጭ ሰዎች ተቀጥሮ፣ የአቶ እስክንድር አባተን ሳይንሳዊ ጥናት ለመስለብ ሲመካክርና እቅድ ሲያወጣ እናያለን። የሚያልቀው ይሄው ቡድን በህግ ቁጥጥር ስር ሲውል እንጂ የእስክንድር ጥናት፣ ተሰፋ እንደሰጠን፣ አባይ ወንዝን አትንኖ ዝናብ ሲያዘንብ አይደለም። ...."ብለህል / እንደህሳብ ስናየው ልክ ሊመስል ይችላል ::አጨራረሱን እንደህንድ ፊልም ያረገውና ተረት ...ተረት ይሆን ነበር ::
::

ይህ የክርክር መስመር ገበያ ያለው አይነት አይደለም። በመሰረቱ ፊልሙ በዋናነት ስለ አባይ መሆኑን የሚያሳስይ ኣባይ ነክ ነገር አላየሁም ስል መጨረሻ ላይ የጥናቱን ውጤት ስላለየሁ ብቻ አይደለም። መሀልም ውስጥ በቲቪና በስእል አባይ ለጥቂት ሴኮንዶች፣ ያውም ከታሪኩ ግንኙነት በሌለው ትእይንት ውስጥ፣ ከመታየቱ በቀር የትልም አካል ሆኖ ታሪኩን ሲያራምድ ሆነ ሲያጣጥፍ፣ ገጸባህሪያቱን ሲያነጋግር ሆነ ሲያጨቃጭቅ አላየሁም። ስለ ውሀ ማትነን ማውራት ስለአባይ ተወራ ማለት አይደለም። የተወራው ለማንኝኘውም ወንዝ ለነጊቤ፣ ፊንጫ፣ ሚሲሲፒ አማዞን ሊሆን ይችላል። ኣባይን ልዩ ያደረገ ነገር የለም።

Quote:
ከቀማኞች መትረፉን ካሳየህ ቀጣዩ የተመልካች ግምት መሆን አለበት ::ለተመልካቹ የሆነ የቤት ስራ ካልተወ ምኑ ነው ትውስታው ?ለምሳሌ በዕኔ ግምት ቀማኛ ከሌለ እንቅፋት ከሌለ ተግባር ላይ ይውላል እላለሁ ::አንተ ደግሞ ሌሎች ቀማኞች ቢነሱበትስ ትላለህ ......ይሄ ነ የቤት ስራው

እኔ ሌሎች ቀማኝኞች ቢነሱበትስ አልልም። እሱ ችግር ከአሁን በሁዋለ በጥበቃ ይፈታል። ጥናቱ ላይ ነው የኔ ጥያቄ። ጥናቱን በተግባር ለመተርጎም ብዙ ነገር እንደሚያስፈልግ ጥቂት ነጥቦች ልጥቀስ .

1 ጥናቱ እስካሁን የልተደረሰበት ጥበብ መሆኑ ስለተነገረን
2 ጥናቱ መቶ በመቶ እንዳልተጠናቀቀ እስክንድር ራሱ መናገሩ፣
3 መሳካቱን እንደሚጠራጥር ለፍሬስላም መንገሩ

እነዚህ ነጥቦች የሚያሳድሩብን ጥያቄ አለ ? ይሳካለት ይሆን ? የሚል ጥያቄ። ደራሲው ምናልባት ለልብ ሰቀላ የተጠቀመበት ዘዴ ሊሆን ይችላል። ከሆነም ደግሞ የጉዳዩን መጨረሻ ማሳየት ይኖርበታል። የቤት ስራ ምናልባት ንኡስ ትልሞች ላይ ይሰራ ይሆናል። ዋናው ትልም ላይ ግን ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘት አለባቸው።

እነ ተሾም ለእስክንድር ጥናት ትልቁ ችግር አይደሉም። ፊልሙ ወደ ማብቂያው እስኪቀረብ እስክንድር ራሱ እነተሾመ መኖረቸውንም አያውቅም። ለስክንድር ትልቁ ጭንቀት የጥናቱ መሳካት፣ አለመሳከት ነው።
ሶላር ኤኔርጂ ባሻህ ጊዜ የምታገኘው የሀይል ምንጭ አለመሆኑ፣
ውሃን ካተነንክ በሁዋላ መጨበጪያ ከሌለው ንፋስ ጋር የሚደረገው "ትግል "፣
ከዳመነልህስ በሁዋላ በፈለክው ክልል ማዝነብ፣

እነዚህ እነተሾመን ስላስወገድክ ብቻ የሚፈቱ ችግሮች አለመሆናቸውን የሚየውቅ ተመልከች ባለበት ዘመን አጨራረስህን እንደ አጀማመርህ ካላሳመርክ ለመበረታተት ያህል የሚሰነዘሩ በጎ ቃላት ብቻ፣ አይደለም አበይን የቴራን ወንዝ አያሻግርም።

ባሻ ይህን አጭር ትይንት ላስታውስህ ,

እነተሾመ በቁጥጥር ስር ናቸው። ታስረው መኪና ውስጥ ይታያሉ። አንድ ጄኔራል ወታደራዊ እንደለበሱ እስክንድርና ፍሬ ከቆሙበት ድረስ መጥተው የክብር ሰላምታ ከሰጡ በሁዋለ ወደ መኪናቸው ይመለሳሉ። እስረኞቹ ሲወሰዱ እስክንድርና ፍሬ ቆመው እስከ መጨረሻ ይመለከቱና ፊልሙ ያልቃል። ይህ አጨራረስ፣ ፊልሙ ለወንጀሉ ክፍል ክብደት እንደሰጠው ከሚያመሳክሩ ትእይንቶች አንዱ ነው።

በእንጻሩ ሌላ ትይንት በአይነ ህሊናህ ተመልከት፣

እስክንድር፣ የተቋዋረጠ ጥናቱን ሲቀጥል፣ ፍሬ ስታግዘው ትንሽ ካየን በሁዋላ አንድ ደርቆ የነቃቃ በጣም ሰፊ የእርሻ መሬት፣ ሳር ቅጠል ያረረበት ጋራ፣ ሰው ከእንሰሳ አጥንቱ ያገጠጠበት መንደር ማሳየት፣
ከዚያ ሰማይ ሲዳምን፣ ሲነጉድና ሲዘንብ
በዝናቡ ምድር ስትለመልም፣ በሺ የሚቆጠር ህዝብ መስክ ላይ ወጥቶ፣ ወደ ሰማይ እያየ ሲጨፍር፣ እስክንድርና ፍሬ መስኩ ላይ , ከህዝቡ ጋር በዝናብ ርሰው "አባይ ተንኖ " የሚልውን መዝሙር እየዘመሩ ፊልሙ ቢጨርስ፣

በኔ እምነት ታሪኩ ሙሉ ክብ ባይሆንም ትንሽ አቅጣጫው ይቀና ነበር ብዬ እገምታለሁ።

የሚቀጥለው ግምገማዬ በቃለ ባህሪያት DIALOG ላይ ይሆናል።
በቅርብ እመለሳለሁ።

ፓስወርድ

---

ሠላም ማለፊያ ቃል

እጅግ ረቂቅ የሆነ ምልከታህን ሳላደንቅ ባልፍ የጥበብ አድባር ትጣላኛለች ብዬ ዛሬ ብቅ ልኩኝ : ባረፍድም ::
እንደዚህ ዓይነቱን ድንቅ ቅኝት ቀድመው አግኝተው ቢሆኑ ስንቶቹ የተሳካለት ስራ በሠሩ : እናም ጊዜ ላንተ አድልታልህ ብዙ ብዙ በቃኝህ ብዬ ተመኘው ::

ከብዙ ብዙ ማክበር ጋር ::

---

ክፍል ሶስት ጭውውት (ቃለ ባህሪ ) Dialogue

Quote:

"የሚወዱኝ ይመስልሻል ?"

"ዘካር ......መውደዱ የኔ ድርሻ ነው ። የነርሱ ድርሻ ልጃቸው የወደደችውን መተዋወቅ ብቻ ነው ::"

ውብ ቃለ -ባህሪ የተናጋሪውን ነፍስ የሚያሳይ መስኮት ነው ይባላል። ከላይ የተጠቀሰው ከጥላ አልበ የተቀነጨበ ነው። በአድማጭ ወይም በአንባቢ የትውስታ ማህደር ውስጥ ቦታ ይዞ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ አባባል ነው ብል ማጋነን አይሆንም። ውብና ልዩ የሚያደርገው ለጥያቄ ቅልብጭ ያል ጥሩ መለስ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ቋዋንቋዋው ቀላልና ግልጽ በመሆኑም ነው።

መልሱ ከጥያቄው ልክክ ብሎ ስለሚገጥም እውነት ይመስላል። ህዝብ ጆሮ ቢደርስ ወዲያው ለቀም የሚደረግና በሰፊው መባል የሚጀምር አይነት ይመስለኛል። catch phrase እንደሚሉት አይነት።

ቃለ -ባህሪ ወይም ጭውውት እውነት መምሰል አለበት፣ በተራው ጊዜ እንድምናወራው፣ እንድምንለፈልፈው፣ እንድምንጨቃጨቀው፣ እንድምንተባተበው፣ እንድምንጨኸው። ለምሳሌ ያህል ከድያና "አጅሬው " የጨለፍኩትን እንመልከት
Quote:

'ዲዬ !'
'አቤት '
'አመንሽኝ እንዴ ?'
'ምኑን ?'
'ስለ ታዲ የነገርኩሽን ?'
'እንዴ !'
'ዛሬ ቀኑ ምንድነው ?'
'ምንድነው ?'
'ምስኪን ዲዬ በጠበጥኩሽ አይደል ?'
'ጆኒ የቀልድህን ሆኖ ከሆነ አንተን አያርገኝ እንዲህ አይነት ቀልድማ አትቀልድም !'
'አልቀለድኩም !'
'ታዲያ !'
'በቃ ቀኑን አስታውሺና እነግርሻለሁ ::'
'ቅዳሜ ነዋ !'
'ሌላስ ?'
'በል አትለፋደድብኝ ልተኛበት ::'
'እስካሁን አልነቃሽም ?'
'ምንድነው እሱ ጆኒ ? ከነገርከኝ ንገረኝ ያለዚያ ግን ደክሞኛል ልተኛበት !'
'April the fool!'

ፍሰቱን፣ ቀላልነቱንና እውነት መሳይነቱን ያስተውሉዋል። ሳንበው ከውኑ ዓለም በቴፕ የቀዳችው ይሆን እስከማለት ነበር የደረስኩት።

የፊልም ባህሪያትም እንዲያ ነው መነጋገር ያለባቸው። ሰማያዊ ፈረስ ውስጥ የሚደነቅ ጭውውት አድምጫለሁ። እስክንድርና ፍሬስላም በሚገናኙባቻው ትይንቶች፣ በአብዛኛው ማለት ይቻላል፣ የሚነጋገሩት ቃል እንከን ላወጣበት አልቻልኩም፣ በተለይ የሆቴሉ በረንዳ ትይንቶች ውስጥ ያለው ጭውውት ተፈጥሮዋዊና እውነት መሳይ ነው።

ጭውውታቸውን እውነት ካስመሰሉት ዘዴዎች አንዱ፣ አንዱ ሲናገር ሌላው አቋዋርጦ የሚገባው፣ ነገር ነው። በውኑ ኣለም እንደምናደርገው ማለት ነው። ይህ ዘዴ ጭውውቱን የተሸመደደ የተውኔት ቃል አያስመስለውም። የተዋኒውንም ብቃት የሚፈትን ነው። ስራዊትና

ዝናሽ በዚህ ረገድ ድርሻቸውን በሚገባ እንደተወጡ አያጠያይቅም።

ተሾምም ከባለቤቱ ጋር የሚነጋገረው ጭውውት ቀንጆ ነው።

ለምሳሌ . የመኝታ ቤቱ ትይንት እንውሰድ።

መኝታ ቤት፣ ተሾመና ባለበቱ ሊተኙ አልጋ ላይ ወጥተዋል

ቅድስት
ምን ታስባለህ ተሼ፣ ችግር አለ እንዴ ?

ተሾም
ችግር ጠፍቶ ያውቅ ይመስል፣ ምን ትጠዪቂኛለሽ

ቅድስት
እረ ተመስገን፣ ምንም አልጎደለ

ተሾመ
አንቺማ ምን ይገበሻል

ብሎ ተሾመ ፊቱን አዙሮ ይከናነባል።

ቅድስት
በል ፊትህን አታዙርብኝ

ተሾመ በመሰለቸት እየዞረ
እፍፍፍ ይኸው።

በማለት ከሁብቱ በስተጀርባ ያለውን ሰላምና ፍቅር አልባ፣ የተሰላቸ ህይወት ማንጸባረቅ ችሎአል።

ሌሎችም ግሩም ጭውውቶች አሉ። ለምሳሌ ጴጥሮስ ከሚስቱና ከልጁ ጋር፣ እንዲሁም መላኩ ከሚስቱ ጋር። ተቃራኒ ጾታዎች መሀል የተደመጠው ጭውውት የሚደነቅ ሲሆን፣ በአንጻሩ በወንዶች መሀል የነበረው ድክመት ነበረበት። አንዳንድ ትይንቶች ላይ የሚደመጡት ጭውውቶች እውነታን የሚየንጸባርቁ፣ የገጸ ባህሪያትን ማንነት የሚገልጡ ወይም ተሪኩን የሚያራምዱ ናቸው ማለት ያስቸግራል።

ይቀጥላል

---

ወዳጄ ፓስወርድ ቀናነት ለተሞላው ምላሽህ አመሰግናለሁ ::የግምገማ ግምገማህን ወደድኩት ስርአት ያለው ነው ::
".....ይህ ለትችቱ መንደርደሪ እንዲሆን ያስቀመጥኩት ....."ብለሀል ::ግምገማ ነው ትችት ?
/ሂስ / ማብራሪያ ካልፈለክና መንደርደሪያ ከሆነ በጥያቄ ነበር መቀመጥ ያለበት ?
"......ይህ የክርክር መስመር ገበያ ያለው አይነት አይደለም። በመሰረቱ ፊልሙ በዋናነት ስለ አባይ መሆኑን የሚያሳስይ ኣባይ ነክ ነገር አላየሁም ስል መጨረሻ ላይ የጥናቱን ውጤት ስላለየሁ ብቻ አይደለም። መሀልም ውስጥ በቲቪና በስእል አባይ ለጥቂት ሴኮንዶች፣ ያውም ከታሪኩ ግንኙነት በሌለው ትእይንት ውስጥ፣ ከመታየቱ በቀር የትልም አካል ሆኖ ታሪኩን ሲያራምድ ሆነ ሲያጣጥፍ፣ ገጸባህሪያቱን ሲያነጋግር ሆነ ሲያጨቃጭቅ አላየሁም። ስለ ውሀ ማትነን ማውራት ስለአባይ ተወራ ማለት አይደለም። የተወራው ለማንኛኘውም ወንዝ ለነጊቤ፣ ፊንጫ፣ ሚሲሲፒ አማዞን ሊሆን ይችላል። ኣባይን ልዩ ያደረገ ነገር የለም።
......."
ማለት የፈለከው የተምታታ ሀሳብ ነው ::ወም ያልተረዳኸው ::የእስክንድር ጥናታዊ ጽሁፍ ለታሪኩ ጭብጥ ይሁን እንጂ ግዴታ አባይ ....አባይ .... የሚያሰኝ ነገር የለም ::ምክንያት የአንድ ፊልም ታሪክ በገንዘብ ጉዳይ መገዳደል ቢሆን ግዴታ ገንዘቡ መታየት ላይኖርበት ይችላል ::መኖሩ በመነገር ብቻ ያልፋል ::ጥናታዊ ጽሁፉ ለታሪኩ ጡዘት /እሽክርክሪት /እንጂ የተጠቀመበት ጠለቅ ያለ ትንተና የለውም ::የፊልሙም ይዘት ወንጀል ነክ እንጂ ሳይንስ ነክ አይደለምና ይህ መከራከሪያ መሆን የለበትም ::
"...........ውሃን ካተነንክ በሁዋላ መጨበጪያ ከሌለው ንፋስ ጋር የሚደረገው ትግል ከዳመነልህስ በሁዋላ በፈለክው ክልል ማዝነብ እነዚህ እነተሾመን ስላስወገድክ ብቻ የሚፈቱ ችግሮች አለመሆናቸውን የሚያውቅ ተመልከች ባለበት ዘመን አጨራረስህን እንደ አጀማመርህ ካላሳመርክ ለመበረታተት ያህል የሚሰነዘሩ በጎ ቃላት ብቻ፣ አይደለም አበይን የቄራን ወንዝ አያሻግርም ..........."ቃላት ውበትም ለስነጽሁፍ ድምቀትም መሆናቸውን አትርሳ ::ለሌላው አገላለጽህ አመሰግናለሁ ::
"........ ፊልሙ ለወንጀሉ ክፍል ክብደት እንደሰጠው ከሚያመሳክሩ ትእይንቶች አንዱ ነው። ............."አዎ የምርምር ስላልሆነ ወደወንጀሉ ያደላል ::በሌላ በኩል መደምደሚያ ያረካትን ሀሳብ እጋራሀለሁ ::ደራሲው ላይቀበል ይችላል ::
""................በእንጻሩ ሌላ ትይንት በአይነ ህሊናህ ተመልከት
እስክንድር፣ የተቁዋረጠ ጥናቱን ሲቀጥል፣ ፍሬ ስታግዘው ትንሽ ካየን በሁዋላ እንድ ደርቆ የነቃቃ በጣም ሰፊ የእርሻ መሬት፣ ሳር ቅጠል ያረረበት ጋራ፣ ሰው ከእንስሳ አጥንቱ ያገጠጠበት መንደር ማሳየት፣
ከዚያ ሰማይ ሲዳምን፣ ሲነጉድና ሲዘንብ
በዝናቡ ምድር ስትለመልም፣ በሺ የሚቆጠር ህዝብ መስክ ላይ ወጥቶ፣ ወደ ሰማይ እያየ ሲጨፍር፣ እስክንድርና ፍሬ መስኩ ላይ , ከህዝቡ ጋር በዝናብ ርሰው "አባይ ተንኖ " የሚልውን መዝሙር እየዘመሩ ፊልሙ ቢጨርስ ........"ቢሆን እመርጣለሁ ::ቀጣይ ግምገማዎጭ ላይ እመለሳለሁ ለእስካሁኑ አድናቂህ ነኝ ::

የሚቀጥለው ግምገማዬ በቃለ ባህሪያት DIALOG ላይ ይሆናል።
በቅርብ እመለሳለሁ።

ፓስወርድ

ካለፈው የቀጠለ

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት አንዳንድ ትይንቶች ላይ የሚደመጡት ጭውውቶች እውነታን የሚያንጸባርቁ፣ የገጸ ባህሪያትን ማንነት የሚገልጡ ወይም ታሪኩን የሚያራምዱ ናቸው ማለት ያስቸግራል፣ ያልኩበትን አንድ ሁለት ምክንያቶች ላስቀምጥ። የመጀመሪያው በጀማሪ ልብወለድ ደራሲያን ስራ ላይ ጭምር የሚታየው፣ ገጸ ባህሪን የተናገረው በማስመሰል ደራሲው ራሱ የሚሞጅረው እንጨት እንጨት የሚል ቃል ነው።

ለምሳሌ
ተሾመ ከጉዋደኞች ጋር
Quote:
ለንድን ውስጥ ሀያ አራት ሰዓት የሚሰራው ሰው ትእዛዝ ብቻ ነው የሚጠብቀው

ሌላ ሃያ አምስት ሰዓት የሚሰራ ከሌል በቀር አባበሉ አይጥምም።

የመላኩ ሚስት
Quote:
ትንሽ ከባህላችን ያፈነገጠ ፊልም ማየት አምሮኛል፣
በባልና ሚስት መሀል የማይዘወተር ወገኛ አባባል።

ተሾመ በስልክ ለሆቴሉ እስተናጋጅ፣
Quote:
የእስራኤል ግርፍ መሆንህን አትርሳ

ደረሲው፣ ለተመልካቹ ስለአስተናጋጁ የእስራኤል ግርፍነት ሊነግረን ስለፈለግ እንጅ፣ ለራሱ የእስራኤል ግርፍ ለሆነው ሰው፣ እንዲህ አይባልም። ምናልባት በግርምታ ወይም በጥያቄ መልክ ቢባል ይመች ይሆናል።
ምሳሌ
የእስራኤል ግርፍ አልነበረም እንዴ የተባልከው፣ ምን ያንከረፍፍህል ?

እንዲህ አይነቱ አባባል ደራሲው ለተመልካች ተጨማሪ መረጃ ለማስተላለፍ በሚፈልግበት ጊዜ የሚከሰት ስህተት ነው። ተዋኒያኑ ፊልም ሲሰሩ ተመልከች እንዳለ እያወቁ ቢሆንም፣ ገጸበህሪያቱ ግን ከራሳቸው አለም ሌላ እንደሌለ ነው የሚኖሩት። የሚያናግሩት ሰው እንዲገባው እንጂ፣ ተመለካች ወይም አንባቢ እንዲገባው ብለው አፍረጥርጠው አይናገሩም። መኖሩንም እንደማያውቁ ነው መሆን ያለባቸው።

ሌላ ሳልተችበት ማለፍ የማልፈልገው ነገር አለ። ይኸውም አስቂኝ፣ ቁምነገር ወይም ትምህርታዊ ወይም ሲናገሩት እንደ ጥቅስ የሚጥም ቃለ ባህሪ ከትረካው፣ ወይም ከትልሙና ከሴማው፣ ማለትም የፊልሙ ሁለንተነዊ መንፈስ ጋር የማይያያዝ ከሆነ ማስወገድ ሲገባ ይባስ ብለው ሲደጋግሙት መስማት ያናድዳል።

ለምሳሌ

Quote:

እንደ አጼ ቴዎድሮስ ጠጣው

ይህ ሀርግ በአስቂኝ መልኩ ይሁን በተረብ ብቻ ከአንድም አራት ገጸባህሪያት ብለውታል። መጀመሪያ ተሾመ፣ ቀጥሎ ጴጥሮስ፣ ከዚያ ልጇ ሳሮንና እናትዋ። አባባሉን ከታሪኩ አንጻር ሳየው ቤት አልመታልኝም። እንደ አስቂኝ ከሆነም ሞኝ ተራ የሚገለፍጥ ይኖር እንደሆ አለውቅም። በኔ እምነት ግን አጼ ቴዎድሮስ መሳለቂያ የሚሆኑበት ዘመን ገና አልደረሰም። የመቅደላው መስዋእትነት ለብዙዎች የጀግንነት አርዓያ ነው። በትግል ላይ ላል ህዝብ ደግሞ የጽናትና የቆራጥነት ምሳለነቱ ያቀመ ነው። የአጼ ቴዎድሮስ አነሳስ፣ ተጋድሎና አማሙዋት በኢትዮጵያ ታሪክ ራሱን የቻል የክብር ቦታ አለው። አንድ ቀን ፊልም እንደሚሰራበትም አልጠራጠርም።

የታሪክ መምህር ተክለጻድቅ መኩሪያ የቴዎድሮስ ገድል "ዘላልማዊና አንጸባራቂ ስፍራ ይዞ የሚኖር፣ የተከተታይ ትውልድ ጥልቅ አክብሮት ሊለየው የማይገባ አኩሪ ቅርስ ነው፣ " ብለውታል፣ አጼ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት በሚለው መጽሀፋቸው፣ ገጽ 13። እና ሲቀለድም የህዝብና የታሪክ እሴቶችን እንዳናራክስ እየተስተዋለ መሆን አለበት፣ አልያ ሳንሱር ሊያስፈልግ ነው።

በመጨረሻ እንደምክር ጣል የማደርገው ነገር ቢኖር፣ ቃለ ባህሪያትን ለማሻሻል ወይም ለማረም ጨክ ብሎ ማገበብ ይጠቀማል። ስታነበው ካስቸገረ ችግር እንደ አለበት ምልክት ነው። ተዋኒያኑ ራሳቸው ቢያነቡት ደግሞ የጠራ ስራ መስራት ይቻላል ባይ ነኝ።

---

ካለፈው የቀጠለ

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት አንዳንድ ትይንቶች ላይ የሚደመጡት ጭውውቶች እውነታን የሚያንጸባርቁ፣ የገጸ ባህሪያትን ማንነት የሚገልጡ ወይም ታሪኩን የሚያራምዱ ናቸው ማለት ያስቸግራል፣ ያልኩበትን እንድ ሁለት ምክንያቶች ላስቀምጥ። የመጀመሪያው በጀማሪ ልብወለድ ደራሲያን ስራ ላይ ጭምር የሚታየው፣ ገጸ ባህሪን የተናገረው በማስመሰል ደራሲው ራሱ የሚሞጅረው እንጨት እንጨት የሚል ቃል ነው።

ለምሳሌ

ተሾመ ከጉዋደኞች ጋር

Quote:

ለንድን ውስጥ ሀያ አራት ሰዓት የሚሰራው ሰው ትእዛዝ ብቻ ነው የሚጠብቀው

ሌላ ሃያ አምስት ሰዓት የሚሰራ ከሌል በቀር አባበሉ አይጥምም።

የመላኩ ሚስት
Quote:
ትንሽ ከባህላችን ያፈነገጠ ፊልም ማየት አምሮኛል፣

በባልና ሚስት መሀል የማይዘወተር ወገኛ አባባል።

ተሾም በሰልክ ለሆቴሉ እስተናጋጅ፣
Quote:
የእስራኤል ግርፍ መሆንህን አትርሳ

ደረሲው፣ ለተመልካቹ ስለአስተናጋጁ የእስራኤል ግርፍነት ሊነግረን ስለፈለግ እንጅ፣ ለራሱ የእስራኤል ግርፍ ለሆነው ሰው፣ እንዲህ አይባልም። ምናልባት በግርምታ ወይም በጥያቄ መልክ ቢባል ይመች ይሆናል።
ምሳሌ
የእስራኤል ግርፍ አልነበረም እንዴ የተባልከው፣ ምን ያንከረፍፍሀል ?

እንዲህ አይነቱ አባባል ደራሲው ለተመልካች ተጨማሪ መረጃ ለማስተላለፍ በሚፈልግበት ጊዜ የሚከሰት ስህተት ነው። ተዋኒያኑ ፊልም ሲሰሩ ተመልከች እንዳለቸው የሚያወቁ ቢሆንም፣ ገጸበህሪያቱ ግን ከራሳቸው አለም ሌላ እንደሌለ ነው የሚኖሩት። የሚያናግሩት ሰው እንዲገባው እንጂ፣ ተመልካች ወይም አንባቢ እንዲገባው ብለው አፍረጥርጠው አይናገሩም። ተመልካች መኖሩንም እንደማያውቁ ነው መሆን ያለባቸው።

ሌላ ሳልተችበት ማለፍ የማልፈልገው ነገር አለ። ይኸውም አስቂኝ፣ ቁምነገር፣ ትምህርታዊ ወይም ሲናገሩት እንደ ጥቅስ የሚጥም አባባል ወይም ቃለ ባህሪ ከትረካው፣ ወይም ከትልሙና ከሴማው ማለትም የፊልሙ ሁለንተነዊ መንፈስ ጋር የማይያያዝ ከሆነ ማስወገድ ሲገባ ይባስ ብለው ሲደጋግሙት መስማት ያናድዳል።

ለምሳሌ
Quote:
እንደ አጼ ቴዎድሮስ ጠጣው

ይህ ሀረግ በአስቂኝ መልኩ ይሁን በተረብ ,ብቻ ከእንድም እራት ገጸባህሪያት ብለውታል። መጀመሪያ ተሾመ፣ ቀጥሎ ጴጥሮስ፣ ከዚያ ልጁ ሳሮንና እናትዋ። አባባሉን ከታሪኩ እንጻር ሳየው ቤት እልመታልኝም። እንደ አስቂኝ ከሆነም ሞኝ ተራ የሚይገለፍጥ ይኖር እንደሆ አለውቅም። በኔ እምነት ግን አጼ ቴዎድሮስ መሳለቂያ የሚሆኑበት ዘመን ገና አልደረሰም። የመቅደላው መሰዋእትነት ለብዙዎች የጀግንነት አርዓያ ነው። በትግል ላይ ላል ህዝብ ደግሞ የጽናትና የቆራጥነት ተምሳሌነቱ የቆመ ነው። የአጼ ቴዎድሮስ አነሳስ፣ ተጋድሎና አሟሟት በኢትዮጵያ ታሪክ ራሱን የቻል የክብር ቦታ አለው። አንድ ቀን ፊልም እንደሚሰራበትም

አልጠራጠርም።

የታሪክ መምህር ተክለጻድቅ መኩሪያ የቴዎድሮስ ገድል "ዘላልማዊና አንጸባራቂ ስፍራ ይዞ የሚኖር፣ የተከተታይ ትውልድ ጥልቅ አክብሮት ሊለየው የማይገባ አኩሪ ቅርስ ነው፣ " ብለውታል፣ አጼ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት በሚለው መጽሀፋቸው፣ ገጽ 13። እና ሲቀለድም የህዝብና የታሪክ እሴቶችን እንዳናራክስ እየተስተዋለ መሆን አለበት፣ አልያ ሳንሱር ሊያስፈልግ ነው።

በመጨረሻ እንደ ምክር ጣል የማደርገው ነገር ቢኖር፣ ቃለ ባህሪያትን ለማሻሻል ወይም ለማረም ሲያስፈልግ ጨክ ብሎ ማንበብ ይጠቅማል። ስታነበው ካስቸገረ ችግር እንደ አለበት ምልክት ነው። ተዋኒያኑ ራሳቸው ቢያነቡት ደግሞ የጠራ ስራ መስራት ይቻላል ባይ ነኝ።

---

ካለፈው የቀጠለ

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት አንዳንድ ትይንቶች ላይ የሚደመጡት ጭውውቶች እውነታን የሚያንጸባርቁ፣ የገጸ ባህሪያትን ማንነት የሚገልጡ ወይም ታሪኩን የሚያራምዱ ናቸው ማለት ያስቸግራል፣ ያልኩበትን አንድ ሁለት ምክንያቶች ላስቀምጥ። የመጀመሪያው በጀማሪ ልብወለድ ደራሲያን ስራ ላይ ጭምር የሚታየው፣ ገጸ ባህሪን የተናገረው በማስመሰል ደራሲው ራሱ የሚሞጅረው እንጨት እንጨት የሚል ቃል ነው።

ለምሳሌ
ተሾመ ከጉዋደኞች ጋር
Quote:
ለንድን ውስጥ ሀያ አራት ሰዓት የሚሰራው ሰው ትእዛዝ ብቻ ነው የሚጠብቀው

ሌላ ሃያ አምስት ሰዓት የሚስራ ከሌል በቀር አባበሉ አይጥምም።

የመላኩ ሚስት
Quote:
ትንሽ ከባህላችን ያፈነገጠ ፊልም ማየት አምሮኛል፣

በባልና ሚስት መሀል የማይዘወተር ወገኛ አባባል።

ተሾም በስልክ ለሆቴሉ እስተናጋጅ፣
Quote:
የእስራኤል ግርፍ መሆንህን አትርሳ

ደረሲው፣ ለተመልካቹ ስለአስተናጋጁ የእስራኤል ግርፍነት ሊነግረን ስለፈለግ እንጅ፣ ለራሱ የእስራኤል ግርፍ ለሆነው ሰው፣ እንዲህ አይባልም። ምናልባት በግርምታ ወይም በጥያቄ መልክ ቢባል ይመች ይሆናል።

ምሳሌ
የእስራኤል ግርፍ አልነበረም እንዴ የተባልከው፣ ምን ያንከረፍፍሀል ?

እንዲህ አይነቱ አባባል ደራሲው ለተመልካች ተጨማሪ መረጃ ለማስተላለፍ በሚፈልግበት ጊዜ የሚከሰት ስህተት ነው። ተዋኒያኑ ፊልም ሲሰሩ ተመልከች እንዳለቸው የሚያወቁ ቢሆንም፣ ገጸበሀሪያቱ ግን ከራሳቸው አለም ሌላ እንደሌለ ነው የሚኖሩት። የሚያናግሩት ሰው እንዲገባው እንጂ፣ ተመልካች ወይም አንባቢ እንዲገባው ብለው አፍረጥርጠው አይናገሩም። ተመልካች መኖሩንም እንደማያውቁ ነው መሆን ያለባቸው።

ሌላ ሳልተችበት ማለፍ የማልፈልገው ነገር አለ። ይኸውም አስቂኝ፣ ቁምነገር፣ ትምህርታዊ ወይም ሲናገሩት እንደ ጥቅስ የሚጥም አባባል ወይም ቃለ ባሀሪ ከተረካው፣ ወይም ከትልሙና ከሴማው ማለትም የፊልሙ ሁለንተነዊ መንፈስ ጋር የማይያያዝ ከሆነ ማስወገድ ሲገባ ይባስ ብለው ሲደጋግሙት መስማት ያናድዳል።

ለምሳሌ
Quote:
እንደ አጼ ቴዎድሮስ ጠጣው

ይህ ሀረግ በአስቂኝ መልኩ ይሁን በተረብ ,ብቻ ከአንድም አራት ገጸባሀሪያት ብለውታል። መጀመሪያ ተሾመ፣ ቀጥሎ ጴጥሮስ፣ ከዚያ ልጁ ሳሮንና እናትዋ። አባባሉን ከታሪኩ እንጻር ሳየው ቤት አልመታልኝም። እንደ አስቂኝ ከሆነም ሞኝ ተራ የሚይገለፍጥ ይኖር እንደሆ አለውቅም። በኔ እምነት ግን አጼ ቴዎድሮስ መሳለቂያ የሚሆኑበት ዘመን ገና አልደረሰም። የመቅደላው መስዋእትነት ለብዙዎች የጀግንነት አርዓያ ነው። በትግል ላይ ላል ህዝብ ደግሞ የጽናትና የቆራጥነት ተምሳሌነቱ የቀመ ነው። የአጼ ቴዎድሮስ አነሳስ፣ ተጋድሎና አማሙዋት በኢትዮጵያ ታሪክ ራሱን የቻል የክብር ቦታ አለው። አንድ ቀን ፊልም እንደሚስራበትም አልጠራጠርም።

የታሪክ መምህር ተክለጻድቅ መኩሪያ የቴዎድሮስ ገድል "ዘላልማዊና አንጸባራቂ ስፍራ ይዞ የሚኖር፣ የተከተታይ ትውልድ ጥልቅ አክብሮት ሊለየው የማይገባ አኩሪ ቅርስ ነው፣ " ብለውታል፣ አጼ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት በሚለው መጽሀፋቸው፣ ገጽ 13። እና ሲቀለድም የህዝብና የታሪክ እሴቶችን እንዳናራክስ እየተስተዋለ መሆን አለበት፣ አልያ ሳንሱር ሊያስፈልግ ነው።

በመጨረሻ እንደ ምክር ጣል የማደርገው ነገር ቢኖር፣ ቃለ ባሀሪያትን ለማሻሻል ወይም ለማረም ሲያስፈልግ ጨክ ብሎ ማንበብ ይጠቅማል። ስታነበው ካስቸገረ ችግር እንደ አለበት ምልክት ነው። ተዋኒያኑ ራሳቸው ቢያነቡት ደግሞ የጠራ ስራ መስራት ይቻላል ባይ ነኝ።

---

ሁለቴ ላክሁ , ምን ዋጣው . ይሄ ሙከራ ነው .

እንዲነሽ አሁን ደግሞ ስባት አድርጎ አመጣው , ሊያስጠምደኝ ነው ልበል ?

---

ባሻሽብሩ እንደጻፈ(ች)ው:
ወዳጄ ፓስወርድ ቀናነት ለተሞላው ምላሽህ አመሰግናለሁ ::የግምገማ ግምገማህን ወደድኩት ስርአት ያለው ነው ::
".....ይህ ለትችቱ መንደርደሪ እንዲሆን ያስቀመጥኩት ....."ብለህል ::ግምገማ ነው ትችት ? /ሂስ / ማብራሪያ ካልፈለክና መንደርደሪያ ከሆነ በጥያቄ ነበር መቀመጥ ያለበት ?
"......ይህ የክርክር መስመር ገበያ ያለው አይነት አይደለም። በመሰረቱ ፊልሙ በዋናነት ስለ አባይ መሆኑን የሚያሳስይ ኣባይ ነክ ነገር አላየሁም ስል መጨረሻ ላይ የጥናቱን ውጤት ስላለየሁ ብቻ አይደለም። መሀልም ውስጥ በቲቪና በስእል አባይ ለጥቂት ሴኮንዶች፣ ያውም ከታሪኩ ግንኙነት በሌለው ትእይንት ውስጥ፣ ከመታየቱ በቀር የትልም አካል ሆኖ ታሪኩን ሲያራምድ ሆነ ሲያጣጥፍ፣ ገጸባህሪያቱን ሲያነጋግር ሆነ ሲያጨቃጭቅ አላየሁም። ስለ ውሀ ማትነን ማውራት ስለአባይ ተወራ ማለት አይደለም። የተወራው ለማንኛኘውም ወንዝ ለነጊቤ፣ ፊንጫ፣ ሚሲሲፒ አማዞን ሊሆን ይችላል። ኣባይን ልዩ ያደረገ ነገር የለም።
......."
ማለት የፈለከው የተምታታ ሀሳብ ነው ::ወም ያልተረዳኸው ::የእስክንድር ጥናታዊ ጽሁፍ ለታሪኩ ጭብጥ ይሁን እንጂ ግዴታ አባይ ....አባይ .... የሚያሰኝ ነገር የለም ::ምክንያት የአንድ ፊልም ታሪክ በገንዘብ ጉዳይ መገዳደል ቢሆን ግዴታ ገንዘቡ መታየት ላይኖርበት ይችላል ::መኖሩ በመነገር ብቻ ያልፋል ::ጥናታዊ ጽሁፉ ለታሪኩ ጡዘት /እሽክርክሪት /እንጂ የተጠቀመበት ጠለቅ ያለ ትንተና የለውም ::የፊልሙም ይዘት ወንጀል ነክ እንጂ ሳይንስ ነክ አይደለምና ይህ መከራከሪያ መሆን የለበትም ::
"...........ውሃን ካተነንክ በሁዋላ መጨበጨያ ከሌለው ንፋስ ጋር የሚደረገው ትግል ከዳመነልህስ በሁዋላ በፈለክው ክልል ማዝነብ እነዚህ እነተሾመን ስላስወገድክ ብቻ የሚፈቱ ችግሮች አለመሆናቸውን የሚያውቅ ተመልከች ባለበት ዘመን አጨራረስህን እንደ አጀማመርህ ካላሳመርክ ለመበረታተት ያህል የሚሰነዘሩ በጎ ቃላት ብቻ፣ አይደለም አበይን የቄራን ወንዝ አያሻግርም ..........."ቃላት ውበትም ለስነጽሁፍ ድምቀትም መሆናቸውን አትርሳ ::ለሌላው አገላለጽህ አመሰግናለሁ ::
"........ ፊልሙ ለወንጀሉ ክፍል ክብደት እንደሰጠው ከሚያመሳክሩ ትእይንቶች አንዱ ነው። ............."አዎ የምርምር ስላልሆነ ወደወንጀሉ ያደላል ::በሌላ በኩል መደምደሚያ ያረካትን ሀሳብ እጋራሀለሁ ::ደራሲው ላይቀበል ይችላል ::
""................በእንጻሩ ሌላ ትይንት በአይነ ህሊናህ ተመልከት
እስክንድር፣ የተቁዋረጠ ጥናቱን ሲቀጥል፣ ፍሬ ስታግዘው ትንሽ ካየን በሁዋላ እንድ ደርቆ የነቃቃ በጣም ስፊ የእርሻ መሬት፣ ሳር ቅጠል ያረረበት ጋራ፣ ሰው ከእንስሳ አጥንቱ ያገጠጠበት መንደር ማሳየት፣
ከዚያ ሰማይ ሲዳምን፣ ሲነጉድና ሲዘንብ
በዝናቡ ምድር ስትለመልም፣ በሺ የሚቆጠር ህዝብ መስክ ላይ ወጥቶ፣ ወደ ሰማይ እያየ ሲጨፍር፣ እስክንድርና ፍሬ መስኩ ላይ , ከህዝቡ ጋር በዝናብ ርሰው "አባይ ተንኖ " የሚልውን መዝሙር እየዘመሩ ፊልሙ ቢጨርስ ........"ቢሆን እመርጣለሁ ::ቀጣይ ግምገማዎጭ ላይ እመለሳለሁ ለእስካሁኑ አድናቂህ ነኝ ::

---

ባሻሽብሩ እንደጻፈ(ች)ው:

ወዳጄ ፓስወርድ ቀናነት ለተሞላው ምላሽህ አመሰግናለሁ ::የግምገማ ግምገማህን ወደድኩት ስርአት ያለው ነው ::

".....ይህ ለትችቴ መንደርደሪ እንዲሆን ያስቀመጥኩት ....."ብለህል ::ግምገማ ነው ትችት ? /ሂስ / ማብራሪያ ካልፈለክና መንደርደሪያ ከሆነ በጥያቄ ነበር መቀመጥ ያለበት ?

"......ይህ የክርክር መስመር ገበያ ያለው አይነት አይደለም። በመሰረቱ ፊልሙ በዋናነት ስለ አባይ መሆኑን የሚያሳስይ ኣባይ ነክ ነገር አላየሁም ስል መጨረሻ ላይ የጥናቱን ውጤት ስላለየሁ ብቻ አይደለም። መህልም ውስጥ በቲቪና በስእል አባይ ለጥቂት ሴኮንዶች፣ ያውም ከታሪኩ ግንኙነት በሌለው ትእይንት ውስጥ፣ ከመታየቱ በቀር የትልም አካል ሆኖ ታሪኩን ሲያራምድ ሆነ ሲያጣጥፍ፣ ገጸባህሪያቱን ሲያነጋግር ሆነ ሲያጨቃጭቅ አላየሁም። ስለ ውሀ ማትነን ማውራት ስለአባይ ተወራ ማለት አይደለም። የተወራው ለማንኛኘውም ወንዝ ለነጊቤ፣ ፊንጫ፣ ሚሲሲፒ አማዞን ሊሆን ይችላል። ኣባይን ልዩ ያደረገ ነገር የለም።
......."

ማለት የፈለከው የተምታታ ሀሳብ ነው ::ወም ያልተረዳኸው ::የእስክንድር ጥናታዊ ጽሁፍ ለታሪኩ ጭብጥ ይሁን እንጂ ግዴታ አባይ ....አባይ .... የሚያሰኝ ነገር የለም ::ምክንያት የአንድ ፊልም ታሪክ በገንዘብ ጉዳይ መገዳደል ቢሆን ግዴታ ገንዘቡ መታየት ላይኖርበት ይችላል ::መኖሩ በመነገር ብቻ ያልፋል ::ጥናታዊ ጽሁፉ ለታሪኩ ጡዘት /እሽክርክሪት /እንጂ የተጠቀመበት ጠለቅ ያለ ትንተና የለውም ::የፊልሙም ይዘት ወንጀል ነክ እንጂ ሳይንስ ነክ አይደለምና ይህ መከራከሪያ መሆን የለበትም ::

"...........ውሃን ካተነንክ በሁዋላ መጨበጪያ ከሌለው ንፋስ ጋር የሚደረገው ትግል ከዳመነልህስ በሁዋላ በፈለክው ክልል ማዝነብ እነዚህ እነተሾመን ስላስወገድክ ብቻ የሚፈቱ ችግሮች አለመሆናቸውን የሚያውቅ ተመልከች ባለበት ዘመን አጨራረስህን እንደ አጀማመርህ ካላሳመርክ ለመበረታተት ያህል የሚሰነዘሩ በጎ ቃላት ብቻ፣ አይደለም አበይን የቄራን ወንዝ አያሻግርም ..........."ቃላት ውበትም ለስነጽሁፍ ድምቀትም መሆናቸውን አትርሳ ::ለሌላው አገላለጽህ አመሰግናለሁ ::

"........ ፊልሙ ለወንጀሉ ክፍል ክብደት እንደሰጠው ከሚያመሳክሩ ትእይንቶች አንዱ ነው። ............."አዎ የምርምር ስላልሆነ ወደወንጀሉ ያደላል ::በሌላ በኩል መደምደሚያ ያረካትን ሀሳብ እጋራሀለሁ ::ደራሲው ላይቀበል ይችላል ::

""................በእንጻሩ ሌላ ትይንት በአይነ ህሊናህ ተመልከት
እስክንድር፣ የተቁዋረጠ ጥናቱን ሲቀጥል፣ ፍሬ ስታግዘው ትንሽ ካየን በሁዋላ እንድ ደርቆ የነቃቃ በጣም ሰፊ የእርሻ መሬት፣ ሳር ቅጠል ያረረበት ጋራ፣ ሰው ከእንሰሳ አጥንቱ ያገጠጠበት መንደር ማሳየት፣
ከዚያ ሰማይ ሲዳምን፣ ሲነጉድና ሲዘንብ
በዝናቡ ምድር ስትለመልም፣ በሺ የሚቆጠር ህዝብ መስክ ላይ ወጥቶ፣ ወደ ሰማይ እያየ ሲጨፍር፣ እስክንድርና ፍሬ መስኩ ላይ , ከህዝቡ ጋር በዝናብ ርሰው "አባይ ተንኖ " የሚልውን መዝሙር እየዘመሩ ፊልሙ ቢጨርስ ........"ቢሆን እመርጣለሁ ::ቀጣይ ግምገማዎጭ ላይ እመለሳለሁ ለእስካሁኑ አድናቂህ ነኝ ::

---

አዲስ

የት ነበርክ ብያለሁ ??

ዋርካ ውስጥ ገብቼ ሌላ ሰፍ በዬ የማነበው ስላስቻልከኝ አድናቆቴና ምስጋናዬ እጅጉን ከፍ ያለ ነው ::

....." ያ ስንት መናገር የሚችል ዓይን በጥቁር መንፅር ተሸፍኖ ...' እንዴት አይነት አገላለፅ ነው በፈጣሪ :: እንዲያው አድናቆቴን ዋው !!! በየ ማለፉን መርጥኩ ::

እዚህ ፅሁፍ ውስት ገብቼ ባልሞነጫጭር በወደድኩ ነበር ግን አድናቆቴን በትንሹ እንኳ ሳልገልፅ ላለማልፍ

ሄሮን

አንዲህ መሀል እየገባችሁ "ካልሞጫጨራችሁማ " አንባቢ መኖሩስ በምን ይታወቅ ነበር . በቅርብ ግጭት (conflict) በሚባልው ርእሰነገር ላይ እሞጫጭራለሁና አትጥፊ .

አክባሪሽ
___________________

Quote:

Serawit Multimedia Production P.L.C
P.O.Box 17346
Tel. 251-1-62 17 97
Mobile.251-9-212001 / 251-9-24 07 11
http://serawitmultimedia.com/

ገምጋሚ / ፓስወርድ

ከሰማያዊ ፈረስ አንጻር የመጨረሻዎቹ ሶስቱ ርእሰ ነገሮች ማለትም ግጭት፣ ልብ -ሰቀላና ትልም በአንድ ላይ ቢገመግሙ ይመቻል በማለት ሶስቱን በጆሮኣቸው ይዤ አምጥቻለሁ። ግጭት፣ እሱ ከሌለ ልብሰቀላ እንደማይኖር እውቆ፣ ብቻዬን ከልሆነ አልቀርብም ብሎ እንገራግሮ ነበር ግን አንዴ በኩርኩም ስገጨው እሺ ብሎ መጥቶኣል።

ግጭትና ልብሰቀላ ከትልም ስር በቀጥታ ስለሚቀናጁ በትልም እጀምራለሁ።

ትልም በመስረቱ የፊልሙ ታሪክ አወቃቀር፣ እቀራረብና አገላለጥ ነው። የድርጊርትና የሁነቶች ቅደም ተከተልንም ይጨምራል። የታሪኩን መንስኤ መግቢአው ውስጥ፣ በሳቢያው

የመጣውን ነገር፣ ጣጣ ሆነ ጸጋ፣ መሃል ውስጥ፣ ከዚያ ፍጻሜው ደግሞ መደምደሚያው ውስጥ መዋቀር ይኖርበታል።

በመግቢያው ዋናውን ገጸባህሪና አላማውን፣ እንዲሁም እንቅፋት ሊሆንበት የተዘጋጀውን ሰው ሆነ ነገር ማለትም የታሪኩን መንስኤ እናያለን። መሀሉ፣ የፊልሙን ዋና ክፍል ያመላክተናል። እዚህ ክፍል ውስጥ ገጸባህሪው የመጀመሪያውን እንቅፋት ለማለፍ ሲሞክር፣ የባሰ ሌላ ችግር ውስጥ ሲገባ፣ ሲወድቅና ሲገለበጥ፣ ሊነሳ ሲል ሲጠለፍ እያየን ጡዘቱ ላይ እንደርሳለን። ከዚያ መደምደሚያው፣ማለትም የመጨረሻው ክፍል ጡዘቱ የሚረግብበት፣ የተሳሰረው የሚፈታበት፣ ዋና ገጸባህሪ አላማው ላይ መድረሱን ወይም ሳይደርስ መቅረቱን የምናይበት ክፍል ነው። 120 ደቂቃዎች እድሜ የለው ረጅም ፊልም ውስጥ ሩቡን ጊዜ ማለትም 30 ደቂቃዎች ለመግቢያው፣ ግማሹን ማለትም 60 ደቂቃዎች ለመሀሉ ክፍል፣ የመጨረሻውን ሩብ ማለትም 30 ደቂቃዎች ደግሞ ለመደምደሚያው ክፍል ይደለደላል። ይህ ወደ ፊልም ተውኔት ጽሁፍ ማለትም ወደ ስክሪፕት ሲመነዘር በተመሳሳይ የገጽ ቁጥር ይዘረዘራል። 120 ደቂቃዎች የሚወስድ ፊልም፣ ከሞላጎደል 120 ገጽ ይኖረዋል ማለት ነው። ይህ የሚሆነው መደበኛነው የሆሊውድን የአጻጻፍ ዘዬ ስንከተል ነው። በነገራችን ላይ ያን መከተለ ግዴታ አይደለም .

ስማያዊ ፈረስን በዚህ መልክ አስልቼ ልጋልብህ ብለው አሻፈረኝ ብሎኛል። አንዱ ችግሩ ፈረሱ ፊልሙ ከመጀመሩ በፊት ሲጋልብ የቆየ መሆኑ ነበር። መግቢያው ላይ መታየት የነበረበት ትእይንት ፊልሙ ሳይጀመር (off screen scene) የተከሄደ ይመስላል። ፊልሙ ትንሽ ካለፈ በሁዋላ ሲኒማው አዳራሽ ውስጥ ለሚገባ ተመልካች , ብዙ ያለፈበት ይመስለዋል። በአጭሩ መግቢያው እንደ መግቢያ ገጸባህሪያትን ከማሳየት አልፎ የታሪኩን መንስኤ እማቅረቡ ላይ ድክመት አለበት።

ፊልሙ ሲጀምር የምናየው የነተሸመ የመጀመሪየው ስብሰባ በሂደት ላይ ስላለ የወንጀል ሴራ እንጂ በመጀምር ላይ ስላለ ጉዳይ የሚነጋገሩ አይመስሉም። እርግጥ በዚያ መልክ ከተጀመረ በሁዋላ መለስ ብሎ (flash back) ቅድመ ታሪክ ማሰየት ይቻላል። ስ ፈ ግን (flash back) የሚጠይቅ የሩቅ ሀላፊ ታሪክ ስለሌለው ለዚያ እይነቱ አሰራር አይመችም።

መግቢያውን ለማሳመርና የታሪኩን አወራረድ ለማቃናት "ያ ውጭ የለው ወዳጃችን " የሚባለው "አረብ " በስብሰባው በመገኘት፣ ወይም አገር ውስጥ ባለው ቀንስላ አማካይነት በሚስጢር የነተሸመን ተልእኮ ሲያስረዳ፣ አመራር ሲሰጥ፣ የመጀመሪያውን ክፍያ፣ ዶላሩን ሲዘረግፍና ውጤት ለመቼ እንደሚጠብቅ ሲናገር ማሳየት ይገባ ነበር። ሰውየውን መደበቅ ያስፈለገበት ምክንያት አልገባኝም። በአባይ ውሀ ጉዳይ ላይ እንኩዋን እንድን ግለሰብ ግብጽን ራስዋን እንደ አገር መጥቀስ የማይቻልበት ምክንያት የለም። እንዲያው ሌለው ቢቀር በፊልም ስማቸውን መጥራት ያቅተን ? በተረትም አባይን ገድበን መጠጣት ፈራን ? ይሄኔ የኛ ብጤ አንድ ደሃ፣ ወይም አንድ ያገር ልጅ ቢሆን ኖሮ የቁም ስቅሉን ነበር የምናሳየው። እይደል እንዴ ሄሮን ?

ከመስመር ወጣሁ። ልመለስ።
ከላይ የተጠቀሰውን ትይንት በመጨመር የፊልሙ ጊዜ እንዳይራዘም አንዳንድ አላስፈላጊ

ትእይንቶች መሰረዝ የግድ ይል ይሆናል። ስ ፊ ውስጥ የአለኣስፈላጊ ትይንቶች ችግር የሉብንም። ለምሳሌ ይልማ ከቢለን ጋር የታየበት ትይንት ሽጉጥ መታጠቁን ለማሳይት እንደ ቅድመ ጥቆማ የቀረበ ይመስለል። ይልማ ሽጉጡን አውጥቶ አፊትዋ ማስቀመጡ። የጴጥሮስም እንዲሁ። "ሚስቱ ምነው መሳሪያ ይዝህ ልጅ ፊት ማለትዋ። " መሳሪያ ከቀበሌ ጽ / ቤት እስክ ት / ቤት ያለ ዘበኛ ሁላ በሚሽከምበት ማህበረሰብ ውስጥ የነይልማ ሽጉጥ መያዝ "ቢግ ዲል " አይደለም። ዶ /ር ቢለንም እንዲያው ሲያካብዱ ነው እንጂ እንኩዋን ሽጉጥ ታንክም አያሸማቅቃቸውም። ህጻንዋም ቤተክሲያን፣ ትምህርትቤት ወዘተ ስትሄድ ስንት ታጣቂ እንድምታይ የምናውቀው ነው። የነፍጥ አገር ውስጥ ሽጉጥ ብርቅ አይደለም። እነዚህ ትይንቶች ሊያጥሩ ወይም ሊስረዙ ይችላሉ።

የፊልሙ መሃከለኛው ክፍል ታሪኩ የሚዳብርበት ስፍራ ነው። ግን መግቢያው ላይ የታሪኩ መንስኤና የዋናው ገጸባህሪ አላማ በደንብ ካልተቀናበረ , መህል ውስጥ የሚዳብረው የታሪክ መስመር ይምታታል። በኔ እምነት እዚህ ክፍል ውስጥ እስክንድር አላማውን ተግበራዊ ለማድርግ ሲዳክር፣ የተለያይ እንቅፋት ሲገጥመው፣ አንዱን እንቅፋት ሲያልፍ ሌላ የባሰ ሲያደናቅፍው፣ በመጨረሻም ጥናቱ ብቻ ሰይሆን የሱም ህይወት አደጋ ላይ ሲወድቅ እያሳየን እስክ ጡዘቱ ጫፍ መሄድ ነበረበት። በአንጻሩ ፊልሙ ያሳየን የነተሸም እቅድ ወደ ግቡ የሚያዳርሰውን ሂደት ነው። ፍሬስላም እስክንድርን ለማጥመድ፣ በመድህኒት አስተኝታ ጥናቱን ለመስረቅ ስትሞክር፣ እነጴጥሮስ የመንግስት ባለስልጣኖችን ለመያዝ ሲሩዋሩዋጡ ወዘተ ነው የምናየው። እስክንድርን በተመለከት እስከ መጨረሻው ምንም እንቅፋት አይገጥመውም። ገንዘብ፣ ጥበቃ፣ መኪና ካስፈለገም ሄሊኮፕተር የተፈቀደለት ሰው ነው። ሁሉም የሚንስትር መስሪያ ቤቶች የሚጠይቃቸውን ሊፈጽሙለት ቃል ገብተውለታል። ግጭት የሚባል ነገር የለም። ስለሱ በሁዋላ። ለጊዜው ግን ግጭት ከሌለ ታሪክ እንደሌለ ይስተዋል።

መደምደሚየው ከመግቢያና ከመሀሉ የሚዋለድ ስለሚሆን መሀሉ ላይ የተወጠረውን ከማርግብ በቀር ሌለ ነገር ሊያሳይን አይችልም። ስ ፊ መሀል ላይ የተወጠረው የነተሸመ ጉዳይ ነው። ያ ጉዳይ መጨረሻ ላይ ከሸፎ ዘብጥያ ሲወርዱ እናያለን። መሀል ላይ ሲዳብር የነበረው ታሪክ መደምደሚየው ላይ እልባት አግኝቶ ይጠናቀቃል። የስክንድር አላማ ምን ላይ እንደደረስ በቃለ ባህሪ ደረጃ እንኩዋን የምናውቅበት እድል የለም።

በዚህ መልክ የተዋቀረ ታሪክ ውስጥ የግጭትና የልብሰቀላውን ተራ በሚቀጥለው ጽሁፍ እናያለን።

ደህና ቆዩኝ።

ፓስወርድ።

———————————

S M P መልስ አለመስጠቱ ይገርምሽ ይሆናል።

በመሰረቱ አንድ መጽሀፍ፣ ትያትር ወይም ፊልም ሲወጣ ሂስ መሰንዘር ወይም ስሪዉን አለማወደስ በክፋት፣ በምቀኝነትና በቅናት ስለሚተረጎም በስነፐበብ ስራ ላይ ግምገማ ማድረግ በኛ የተለመደ አይደለም። ምን አገባኝነት , ከሰው ምናጣላኝነት ሰፍኖአል .

በአንጻሩ የምናየውና የምንሰማው ጭፍን ውዳሴና ምክንያት የለሽ ሙገሳ ነው። በርካታ መጻህፍትና ፊልሞች ከልካቸው በላይ የተጋነነ ቃለ ውዳሴ ይዘንብባቸውና ሰው ምን ተአምር ተሰራ ብሎ ሲመረምራቸው የሚያስተዛዝቡ ጉዶች ሆነው ይገኛሉ።
አንድ የፐበብ ስራ ህዝብ ዘንድ ከመቅረቡ በፊት ቢገመገምና ጉድለቱ ቢወግድ ግን ውጤቱ የበለጠ እንደሚሆን አልጠራጥርም።

ሁሉም፣ ፑሽኪንን የሚያርም ማን ነው ባይ ከሆነ ስራቸን አቡዋራማ ይሆናል።

ግምገማ የራሱ በጎ ጎን አለው። እሱን እንይ ነው የምለው።

ምን ይመስልሻል። ሀሰብሽን አስኪ አካፊይን።

——————————

ፓስወርድ አንተ እንዳልከው ሚጠቀምበት ካለ ግምገማ የራሱ በጎ ጎን አለው :: ፊልሙን በግጭት፣ ልብ -ሰቀላና ትልም እይታህ ጥሩ ሄደህበታል :: በበኩሌ ፊልሙ የተወራለትን ያህል አላገኘሁትም ይልቅ ከጠበቁት በብዙ መልኩ ወርዶብኛል ::

ሰማያዊ ፈረስ ላይ ሰራዊት ፍቅሬ ከደራሲነት እና አዘጋጅነት በተጨማሪ በአቅረቢነት : የዋናው የፊልሙ ገጸ ባህሪ /እንደ ኢንጂነር እስክንድር አባተ / ሆኖ በመተወን፣ ፊልም ማጀብያ ለተሰራ ዘፈን /Sound track/ ግጥም በመድረስ : ፊልሙን በየፊልም ቤት እያዞሩ በማሳየት Laughing (በሰረዊት ማልቲሚዲያ ፕሮደክሽን ) በፊልም መሀል በተሰሩት ማስታወቂያዎች በመተወን ፣ እና ለነዚህ ማስታወቂያዎች በድምጽ አንባቢ በመሆን ...... ሰርቷል :: ይህንን ችሎታውን እና ልፋቱ ልናደንቅለት ይገባል ::

ሆሊውድ ውስጥ ከሚገኙ ታዋቂ የጥበብ ሰዎች ውሥጥ በጣት ሚቆጠሩ እንደነ ሮቢን ዊልያም እና ኤዲ መርፊ ያሉ ባለዘርፈ ብዙ ክህሎት /Multi-talented/ ሰዎችን እናገኛልን ::
እንደ ኤዲ መርፊ ያለው ሰው ፣ በሲኒማ ትወና ብቻ ሳይሆን ከኮሜድያንነት፣ ሙዚቃ በመሞዘቅ፣ ፊልም በማዘጋጀት ፣ በዳይሬክተርነት ፣ በአንድ ፊልም ላይ ብዙ ገጸ ባህሪያት / multiple roles/ ሆኖ ሲጫወት ሌላውን ክፍተት ሲሞላ እንጂ ሲያጎድል አናየውም :: ምሳሌ ካስፈለገም Nutty proffesor በተባለው ፊልም ላይ የ 7 ሰዎችን ገጸ ባህሪያት / characters/ በብቃት ወክሎ ተጫውቷል :: በቅርቡ ደግሞ Norbit በተባለ ፊልም ላይ 3 ገጸ ባህሪያትን እንዲሁ በብቃት ወክሎ ተጫውቷል :: በተለይ Norbit ፊልም ላይ የወፍራሟን ሴት ባህሪን ወክሎ የሰራው ወንድ መሆኑን ወይም / ኤዲ መርፊ / መሆኑን ማንም አይጠረጥርም በዚህ በጣም ስንገረም በዚሁ ፊልም ላይ ቻይናዊ ሰው ሆኖ የሰራው ከሻንሀይ የመጣ ቻይናዊ ሳይሆን አሁንም እርሱ መሆኑን ስናረጋግጥ ለአድናቆታችን ወሰን እናጣለታለን :: ኤዲ መርፊ በድምጽ ተዋናይነት /voice acter/ ሆኖ ደግሞ Shrek እና

Disney's Mulan የመሳሰሉ ፊልሞች ላይ እናገኘዋለን ::

ወደ ሰማያዊ ፈረስ ፊልም ስንመለሥ ፊልሙ በሲኒማ ቤት በሚቀርብበት ወቅት ላይ ለተሰሩ አላስፈላጊ መስለው ለታዩኝ ሥራዎች ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች ቢከወኑ ከባድ እንደሚሆኑ ይገባኛል :: ሆኖም ለወጪ ቁጠባ ይሁን ሁሉንም እኔ ልቆጣጠር በሚል አባዜ ከዚህ አልፎ አንድን ሰው በአንድ ፊልም አክተርነት ወጥቶ ብዙ አላስፈላጊ ቦታዎች ላይ ማየት የፊልሙን ይዘት እና ደረጃ ያወርደዋል ::

ይህንን ለማለት ያስደፈረኝ ፊልሙ በሲኒማ ቤት ይታይ በነበረበት ወቅት በየመሀሉ ከሚቀርቡት ደንቃራ ማስታወቂያዎች በተጨማሪ ብዙዎቹ ላይ በዋና ገጸ ባህሪነት ላይ የሳልነው ሰራዊት ፍቅሬ /ኢንጂነር እስክንድር አባተ / ታች ወርዶ ማስታወቂያዎች ላይ አዋሽ ፈጥኖ ደራሽ ሲለን ወይም ሌላ ተጨማሪ ማስታወቂያ ላይ ይህን ግዙ ያንን አትግዙ እያለ ሲዋሽን እና አልባሌ ነገር ሲዘባርቅ ስናየው ሚፈጥረው ምስቅልቅል ስሜት ነገር ይታያቹ ::

ይህ ሲገርመን በፊልሙ መሀል ላይ ለሚቀርቡ ማስታወቂያዎች (advertisement) በንባብ እና በትወና ሰራዎች በአብዛኛው ሰራዊት ፍቅሬ ሲተውን እናየዋለን ::

ይህ ደግሞ ፊልሙን ሊመለክት የገባ ተመልካች ብዥታን ብሎም መምታታትን ይፈጥራል :: ያሁኑን አላውቅም ከዛሬ 4 አመት በፊት ምታተ ሳጥን /TV/ ላይ ለሚቀርብ ማስታወቂያ ለሚያነብ ሰው ቢበዛ ሚከፈለው ከ 500 ብር አይበልጥም ነበር :: ሰራዊት ይህንን ከፍሎ ማስታወቂዎችን ማስነበብ ሲችል ሲቆናቆን እናየዋለን :: ስነጥበብ ጎኑ ይልቅ የቢዝነስ ጎኑ ሲያደላ እናስተውላለን ::

ፓስወርድ እንዳለው ፊልሙ እንዳይራዘም ወይም እንዳይንዛዛ አንዳንድ አላስፈላጊ ትእይንቶች እና ንግግሮች መሰረዝ ነበረባቸው :: በእኔ እይታ ገና ለገና ላልተጠናቀቀ ጥናት የሀገሪቱ መሪ እስክንድርን የተካበደ እራት ግብዣ ቤተመንግስት ድረስ መጥራት እና መጋበዝ ለምን እንዳስፈለግ አልታየኝም :: አዲስ አበባ ላይ በብዛት ማናየውን ደረጃ መወጣጫ / Escalator/ ያለቦታው ማሳየት : ፊልሙ ላይ የምናያቸው ቪላ ቤቶች እና የተቀናጡ መኪናዎች፣ ከተማዋ ውስጥ ምናያቸው ቦታዎች ጸዳ ጸዳ ያሉ ብቻ መሆን የአዲስ አበባን እውነተኛ ገጽታ ስላላሳየን ፊልሙን ታማኒነት አሳጥቶታል ::

ለአንድ ግለሰብ ምንም አይነት ውጥረት ሳይኖር ታንክ እና ሄሊኮፐተር ለእስክንድር እንደተመደበ ማውራት ሚሰጠውን ፋይዳ ጎልቶ አልታየኝም :: እንዲሁም መጨረሻ ላይ የነተሸመ ማፍያ ቡድን ለመያዝ አንድ ጀኔራል ትዛዝ ይሰጣል ወይም እነዚህ ግለሰቦች አደጋ ማድረስ በማይችሉበት ሁኔታ ይጎበኛል እንጂ እታች ያለ ቦታው ወርዶ ማፍያዎችን ድረስ ሄዶ እጅ ከፍንጅ መያዝ ሚኖርበት አይመስለኝም ::

ሌላው ፊልሙን ታማኒነት ሚያሳጣው የመጀመርያ ድርሰቷ ያልተሸጠላት ደራሲ በሀገራችን አኗኗር ትልልቅ ሆቴል አልጋ እየተከራየች እንደምትጽፍ ማሳየቱ እኛን እንካን ብናምን ከእንግሊዝ የመጣ ተመራማሪ እንጂነር ይዋጥለታል ማለት ዘበት ነው ::

አዘጋጅ ሰራዊት ፍቅሬ ለፊልም ትወና ቀድሞ በየትያትር ቤቶች ምናቃቸውን እና ኃላም ወደ ማስታወቅያ ሥራ የገቡትን እነ ታምሩ ብርኃኔ ፣ ኪሮስ ኃ /ሥላሴ ፣ ተስፋዬ ገ /ሀና፣ ዝናሽ ጌታቸው፣ ሽመልሥ በቀለ ....መርጧል :: ፊልሙ የቲቪ ማስታወቅያ ሰዎች ስብስብ ቢመስልም የመረጣቸው ተዋንያን የተሰጣቸውን ድርሻ በብቃት ተወጥተዋል ለማለት ቢከብደኝም : አላሳፈሩትም ማለት እችላለሁኝ :: ከነዚህ ውጭ ቀዝቃዛ ወላፈን ላይ የተወነው / ስሙን አላውቀውም / እና ከ ETV/አሰረስ በቀለ / ከጋዜጠኞች ደግሞ /አበበ ፈለቀ / እካቷል :: ፊልሙ የእንግሊዝኛ ሰብታይትል እንዲኖረው ማድረጉ ያስመሰግነዋል :: ሲቀጥል አማርኛ መረዳት ሚያቅተው ወይም እንግሊዝኛ ሚያነብ ሰው በተጨማሪ ሊመለከተው ይችላል ::

እና ሰራዊት ፍቅሬ ድንገት ተሳስተህ ይህንን ጽሁፍ ካነበብክ በሚቀጥለው አዲሱን ፊልምህን ስትሰራ ባለፈው ሲኒማ ቤት ያበሳጨከኝ አንሶ እንደ ኤዲ መርፌ 7 ገጸ ባህሪያት ተላብሰህ ደሜን እንዳታፈለው አደራ ::

ፓስወርድ እንዴት አይነት ድንቅ አርእስት ጀመርክ ? ደሞ እንዴት ጎበዝ የምትጽፈውን በደንብ የምታውቅ ሰው ነህ ? የአንተ አይነት ሰዎች ወደፊልሙ ኢንዱስትሪ ታዲያ ምነው ጠጋ ብላችሁ የተሻለ ነገር በቋንቋችን እንድናይ ብትረዱን ....

እኔ እንኳን ብዙም ልናገር አይደለም የገባሁት ያንተ ግምገማ አንጀቴን አርሶት ቀጥልበት ልልህ ነው :: አገላለጾችህ ድንቅ ናቸው ....ትክክለኛ የአርት ክሪቲክ ነህ ...."ዐባይን በተረት ውስጥ እንኳን መገደብ ፈራን ' ያልከው አገላለጽህ ለምሳሌ እጹብ ድንቅ ነው ...... ራሳቸው እነሰራዊት ይሄን ገጽ እያተመ የሚልክላቸው ካለ ወይም ውጪ ሲወጡ የሚያነቡት ከሆነ ብዙ ይማሩበታል ብዬ አስባለሁ (እዛ ዝግ ስለሆነ ብዬ ነው ):: ሰራዊት በጣም ስጦታ ያለው ተዋናይም ደራሲም መሆኑን ከዚህ በፊት በሌሎች ፊልሞች ለምሳሌ አርስቱ ጠፋብኝ እንጂ ይሄ እናቱን እቤት ሰራተኛ ሆና ደፍሮዋት ከዛም ገድሎዋት (ወይም ገድያታለሁ ብሎ አስቦ ) ልጇን ወስዶ የሚያሳድግበት ፊልም .....እሱ አሁን እያንዳንዱ ገጸ ባህሪ በትክክል የተቀረጸበት ተዋንያኑም አንድ እንኳን ሳይቀር ባህሪዎቻቸውን ፐርፌክትሊ የተላበሱት ፕሎቱ ብትል ዲያሎጉ ብትል .....ብቻ ምንልበልህ እኔ ድሮ ከቲቪ ላይ ቀድቼው አሁንም ቪኤችኤስ ላይ አለኝ ....ኢት ዎዝ ፈርፌክት ነው የምልህ ......እና አሁን እዚህ ላይ ግን ሰራዊት ጥሩ ፕሎት አምጥቶዋል ....ታሪኩና ገጸ ባህሪ አቀራረጹም ከሞላ ጎደል በኔ የባለሞያ ባልሆነ አመላካከት እዛኛው ላይ ባይደርስም ደህና ነው :: ...ግን አንድ ነገር ያስተዋልኩት ፊልሙን ሲሰራ የአንድ ለውጥ ሊያመጣ የተነሳ የውሀ መሀንዲስ ታሪክ ነው .....

........እና ቢያንስ ሰራዊት አንድ መሀንዲስ ወይ ሀይድሮሎጂስት በአማካሪነት ስክሪፕቱን እንዲያይለት በተለይ ይሄ ነው የሚባል ቴክኒካል ዲያሎግ ባይኖርም እንዲኖር ማድረግ እና ያለውንም ዲያሎግ ተአማኒነት እንዲኖረው በጣም ሳይበዛ የተወሰነ ቴክኒካል ነገር ተመልካቹ እንዲሰማ ማድረግ ነበረበት ....... አማካሪ የለውም ያልኩት ለምሳሌ ኢንጅ . እስክንድር ውሀ ልማት ሄዶ ዶክተሩን ሲያናግር .....ከሚጠይቃቸው አስቂኝ ጥያቄዎች መሀከል ...በጣና ሀይቅ እና በፊንጫ ግድብ መሀከል ምን ያህል ርቀት እንዳለ ይጠይቃል .....ይሄ አይነት ቀላል ዳታ ከማፕ ላይ የሚነበብ በዚህ የመረጃና ኢንተርኔት ዘመን ደግሞ ከውጭ ሀገር ተምሮ የመጣ መሀንዲስ ያውም አባይን አትንኖ ሊያዘንብ የሚያስብ (ሀሳቡ በነገራችን ላይ

ኢንጂነየስ ነው ቴክኒካሊ አባይን በኢትዮጵያ አቅም መገደብ እንደሚይቻል ስራዊት የተረዳ ወይም የሰማ ይመስለኛል ) ጂአይ ኤስ እና ሌላው ሶፍትዌር ቢቀርበት በቀላሉ ከኢንተርኔት ጉግል አርዝ እና ኢንካርታ የያዙትን ተራ መረጃ ቢሮ ሄዶ መጠየቁ ትንሽ ተአማኒነት አሳጥቶታል .

....ሌሎችም እንዲሁ ቴክኒካሊ ከዋናው ገጸ ባህሪ ሞያ አንጻር ያስተዋልኳቸው ነበሩ .....ግን አሁን ካየሁት ትንሽ ስለቆየ አላስታውሳቸውም ......ፓስወርድ ቀጥልልን .....አቦ እኛ ገብተን ከምንዘባርቅ እንዳንተ አይነት ባለሞያ ሲናገረው ይሻላል ....የዋርካ ትክክለኛ አላማ እንዳንተ አይነት ታለንቶች መድረክ እንዲያገኙ ማድረግ ነውና በርታ እልሀለሁ ..........

አድናቂህ

ዛዙ

ግጭትና ልብሰቀላ

ግጭት ሰፊ ትርጉም አለው። ከእካላዊ ግጭት እስከ ስሜታዊ ጥላቻ፣ ከራስ ጋር ከመሙዋገት እስከ ከተፈጥሮ ጋር መታገልን ሊያካትት ይችላል። ግጭት የሌለበት ይህወት የለም። ህይወትም ያለ ግጭት አይጥምም። ፊልምም እንደዚያው ነው። ከራስ ጋር፣ ከቤተሰብ ጋር፣ ከስራህ ጋር፣ ከመህበረሰቡ ጋር፣ ከተፈጭሮ ጋር ግጭት አለ። ሁሉም ነገር ልክ እንደምንፈልገው አለመሆኑ ነው፣ ግጭት የምለው።

ሁሉም ልክ እንደምንፈልገው እንዲሆን ለማድረግ የምንጉዋዘው መንገድ፣ አቀበት ቁልቁለቱን፣ ቀናው ጥምዙን ስንዳክር ነው ልብሰቀላው። ግጭቱ ክርር፣ ምርር ያለ ሲሆን ልብሰቀላውም በዚያው ልክ ከፍ ይላል።

ሰ ፈ ውስጥ ዋናው ገጸባህሪ ካሰበው ኣላማ ለመድረስ እንደይችል እንቅፋት የሚሆኑት እነተሾመ መኖራቸው የታሪኩ ዋናው ግጭት ነው። በዚህ ግጭት ምክንያት ነው፣ ተመልካች የስክንድር አላማ ይሳካል ወይስ አይሳካም እያለ በጉግት እስከመጨረሻው የሚጠብቀው። ከዚህ ከዋናው ግጭት ሌላ ቁዋት ሞላ የሚያደርግ ግጭት አላየሁም። አንድ መቶ ሀያ ደቂቃዎች የሚወስድ ፊቸር ደግሞ በአንድ ግጭት ለመዝለቅ መሞከር ..................

እና ምን መደረግ ነበረበት ?
አዎ የዚህ ግምገማ ዋና አላማ ስህተት ጎልጉሎ የሰው ድካም ዋጋ ማሳጣት ሳይሆን፣ ምን መደረግ ነበረበት ? ለሚል ጥያቄ መልስ እየሰጠ የተሻለ ስራ ለመስራት ትንሽ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው።

ግጭት በገጸባህሪ ውስጥ

ግጭት ሰፊ ትርጉም አለው፣ ብያለሁ። በፊልም አለም አንድ ገጸባህሪ በውስጡ የሚብሰለሰል ፍርሀት፣ ጥርጣሬና ከህሊናው ያልታረቀ የጸጸት ስሜት ወዘት ግጭት ይባላል። በዋናዋናዎቹ ገ / ባህሪያት ውስጥ ከታሪኩ ቀዘማጅ የሆነውን ማሳወቅ ያስፈልጋል። ውስጠዊ ግጭት በቃል አንዳንዴም በትዝታዊ ወይም በህልም ትእይንት ውስጥ መግለጽ ይቻላል።

ስክንድር ውስጥ ምን አይነት ግጭት ሊኖር ይችላል ?
በመጀመሪያ ደረጃ የጥናቱ መሳካት ጉዳይ አለ። ባይሳካስ የሚል ፍርሀትና ጥርጣሬ መጫር አለበት። ያን በከፊል ከፍሬስላም ጋር ሲነጋግር ጠቅሶታል። ግን ከዚያ በለይ መሄድ ነበረበት። ባለመሳከቱ ምክንየት በሱ በግሉ የሚደርሰውን ችግርና ውርደት እንድሁም በጥናቱ መሰረት፣ ወደፊት በአገሪቱ ላይ የሚደርሰውን የበረሃማነት መስፋፋት፣ ወይም ደርቅ መሰል አደጋ መከሰትንና የብዙ ሰው ህይወት ከባድ አደጋ ላይ እንደሚወድቅ በአጽንኦት ማውሳት ነበረበት።

እነተሾመም እንደ ሰው በውስጣቸው ግጭት አለ። ለግሉ ጥቅም ሲል የሀገርን ጭቅም የሚጻረር ነገር የሚፈጽም ሰው ህሊናው ጋር ሙግት መግጠሙ አይቀርም። ለዚህም ነው ተሾመና ናደው ፣ በስድስት ሚሊዮን ዶላርና በእናት ሀገር ጥቅም መሀል ያለውን ጉዳይ ያነሱት።
Quote:

ተሾመ
ስድስት ሚሊዮን እንኩዋን እናት አገረ ወላጅ እናት ያስክዳል

ናደው
እሱ እንደተሸከመው ህሊና ነው።

እነዚህ ሰዎች ይህን ወንጀል እንዲፈጽሙ ያንሳሳቸው ዋናው ምክንያት ግልጽ አልሆነልኝም። ብዙ ሚሊዮን ብር ያፈሰሱበት ድርጅታቸው ከባድ ኪሳራ ላይ መውደቁንና በእዳ የሚዘፈቁበት ጊዜ እየተቃረበ ስለመጣ የቅንጠቱ ኑሩ ማብቂያው ታይቶኣቸው ቢሆንስ። ሰው ብዙ ጊዜ ለገንዘብ፣ ለብሩ፣ ብቻ አይደለም ወንጀል የሚሰራው፣ በገንዘቡ መጠበቅ የሚፈልጋቸው እሴቶች አሉት። ቅንጦት የለመደች ሚስት፣ በድሎት ያደጉ ልጆች፣ በገንዘብ የተሸመተ ክብርና ሞገስ ............... ያን ሁሉ ለመጠበቅ አይገቡ ይገባል።

እንዲሁ ገንዘቡን ፍለጋ የሚወናጀልም ጅል ሞልቶአል። ለሱ አይነቱ ታሪክ የገጸባህሪያቱን ተነሳሽነት ተኣማኒ ለማድረግ ብሩን ከነነብሱ በሸንጣ አምጥቶ ማሳየት ነው። ብዙ ገንዘብ ነክ ፊልሞች ውስጥ ዶላሩ በጥቅል በጥቅሉ ሻንጣ ውስጥ ተደርድሮ የምናየው አለምክንያት አይደለም። አንዱ ገጸ ባህሪ ከጥቅሉ አንድ ሁለቱን አንስቶ ሲተረትር የምናየው አልምክንየት አይደለም። ያን ገንዘብ ተመልከቶ ራሱ በልቡ ስለሚመኝ ያን ገንዘብ ለማግኘት ሰዎች የሚፈጽሙትን አሰቃቂ ወንጀልንም ያምናል።
እነተሾመ ስድስት ሚሊዮን፣ ሰላሳ ሚሊዮን እየተባበሉ ከሚያካብዱት እንድ ያሲን አረፋትን የመስለ ቀይ ሰው ከነጥምጥሙ ስብሰባቸው ድረስ እምጥተው አንድ ዶላር የሞላ ሻንጣ አንዴ

ሲከፍት ማሳየት ይበቃል። ፊልም የሚተረከው በምስል እንጂ በቃል አይደለም። ማለትም ታሪኩን በተቻለ በማሳየት እንጂ በመናገር አይደለም የምንገልጸው።

ግጭት በቡድን ውስጥ ወይም ከቡድን ጋር
ይህ እነተሾመን የሚምልከት ርእስ ነው። እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ለቡድኑ ያለው ታመኝነትና አንዱ ለሌለው ያለው አመለካከት ይለያያል። አንዱ ካሸ አሁኑኑ ካልነከስኩ ሲል፣ ሌላው ጥናቱ ሳይጠናቅቅ አክሽን አንውሰድ ይላል። ያን አይነት ግጭት እንዲታይ ሲሆን ይካካዱ ይሆን፣ አንዱ መሀል ላይ ያፈነግጥ ይሆን በሚል ጥያቄ ልብሰቀላ ይፈጠራል።

ለትብብር መገደድ
ቡድን ውስጥ እንዲገባ ወይም የቡድኑን አላማ ሳይወድ ተግበራዊ እንዲያደርግ የሚገደድ ሰው ግጭት ይፈጥራል። ያ ሰው ሁዋላ ምን ያደርግ ይሆን ? የሚል ጥያቄ ይቀሰቅሳል። ፍሬሰላም፣ ቡድኑ የሰው ህይወት እስክማጥፋት እንደሚደርስ ስትሰማ ከቡድኑ ጋር ቅራኔ ውስጥ ትገባለች። ያ ሁሉ በደንብ አልሾልም እንጂ ግጭት ነው።

ግጭት የሚፈጠርበት ብዙ መንግድ አለ። አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ገ /ባ የማይስማሙ ወይም የማይጣጣሙ ግብዎች እንዲኖሩዋቸው በማድረግ፣
- ግብ ብቻ በቂ ስላልሆን፣ ግብን ባለመምታትህ ምክንያት የሚደርሰውን ጣጣ በግልጽ ማሳወቅ
- በገጸባህሪያት መሀል የስልጣን ፉክክር ወይም ለመሾም ጭራ መቁላት የመሳሰለ ባህሪ ማሳየት፣
- ፉክክር፣ ውድድር፣ ግጭሚያ ወዘተርፈ ግጭት ይፈጥራሉ።
- እንድ ተልእኮ የተወሰነ ቦታ ላይ ሲደርስ ወይም ከመድረሱ በፊት እርምጃ መውሰድ፣
- እንድ ተልእኮ በተወሰነ የጊዘ ገደብ እኒጠናቀቅ መወሰን

ስ ፈ ለፍሬሰላም ተልእኮዋን እንድታጠኛቅቅ የሶስት ሳምንት ጊዜ መስጠቱ ከጊዜ ጋር እንድትሩወረጥ ነበር፣ ግን ካሌንደር ስታይ፣ ስትቻኮል አላየሁዋትም። እናም ከጊዜ ጋር ያላት ግጭት ጎልቶ አልወጣም። ስላልወጣ በዚያ ንኡስ ትልም ሊፈጠር የሚችለው ልብ ሰቀላ ቀርቶአል።

ከለይ በጠቀሰኩት መልክ ግጭት ከተፈጠረ በሁዋላ የሚከተለውን ልብሰቀላ በሚቀጥለው ጡፍ፣

እስከዚያ ደህና ቆዩኝ፣

አንባቢዎች አስተየይት ወይም ጥያቄ ብታክሉ ያልተዳሰሰ አውደ ፊልም ውስጥ ሊያስገባን ይችላል። እነባሽብር
የጠቃቅሱትን መሰረት በማድረግ እንደጫጫርነው ማለት ነው።
ዘዙና ሰንድ በዚህ አጋጣሚ ለአስተያየታችሁ አመሰግናለሁ።

____________________________________
http://babile.webs.com/

ፓስወርድ ,

ጥበብ በሞያተኞች ስትጠበብ አቤት !... ብዙ ነገር እየተማርኩበት ነው :: አንተን በአስተማሪነትህ እንዲያበረታህ እየተመኘሁ - ካንተ የሚቃዳውን የጥበብ ምንጭ ፍንጣቂው ሳይጎበኘኝ እንዳያልፍ በአገኘሁት አጋጣሚ በዋርካ መስኮት አንገቴን ብቅ በማድርግ የሚቀጥለውን ግምገማህን ለማንበብ ከረጅሙ ሰልፉ መሃል ቆሚአለሁ ::

አትጥፋሃ ፓስወርድ

አድናቂህ ::

heron እንደጻፈ(ች)ው:
ፓስወርድ ,
- ካንተ የሚቃዳውን የጥበብ ምንጭ ፍንጣቂው ሳይጎበኘኝ እንዳያልፍ በአገኘሁት አጋጣሚ በዋርካ መስኮት አንገቴን ብቅ በማድርግ የሚቀጥለውን ግምገማህን ለማንበብ ከረጅሙ ሰልፉ መሃል ቆሚአለሁ ::

አቦ እንዴት ደስ ይላል። በተራ ቃላት እንዲህ የሰው ልብ መንካት ይቻላል ? የሆነ ነገር ተሰማኝ , ብርታት ነገር .
አመሰግናለሁ ሄሮን።

እቀጥላለሁ። የሚቀጥለው ርእስ የስ ፊን ልብ -ሰቀላ የሚመለከት ይሆናል። ከዚያ አንድ ማጠቃለያ አክልና አበቃለሁ። ሳምንቱ መገባደጃ ላይ እንናበብ። ቻዎ Very Happy

አክባሪ (ህ )ሽ
____________________________________

ልብ ሰቀላ ፣
- የጉዳዩን ጫፍ ብቻ ነግሮ ዋናውን ፍሬ ነገር ለጊዜው መደበቅ
- የፊቱት የሚደርስ በመስመሰል ልብማንጠልጠል፣
- ተመልካችን በግምት አንቲሲፔሽን ማንሳፈፍ፣
- በታሪኩ ውስጥ ለሚነሳ ጥያቄ መልስ ማዘግየት፣
የመሳሰለ ሲሆን በስ ፊ ፊልም ውስጥ ይህ ዘዴ የትኞቹ ትእይንቶች ላይ ተጠቅሞበታል፣ የትስ ሳይጠቀምበት ቀረ ?

ለአብነት ያህል አንድ ሶስት ትእይንቶች እንውሰድ።
1. ፍሬ ሰላም ስክንድርን በመድህኒት ልታስተኛ የወጠነችበት ትይንት ላይ ልብ የሚሰቅል ሁኔታ ብልጭ ብሎ ነበር ግን ድራሲው ከልብ ሰቀላ ይልቅ ታሪክ -አጠፋ (story twist)

በመምረጡ ስቀላው ባጭር ተቀጭቶአል። ስክንድር የፍሬን ፎን ለማምጣት ሲወጣ ክኒኑን እቦርሳዋ ውስጥ ፈልጋ በማጣትዋ ምክንያት ያሰበችው ሳይሳካ ይቀራል።

ክኒኑ ቢኖርና ስክንድር ወጣ ሲል መጠጡ ውስጥ ብትከተው ልብሰቀላ የሚዘየድበት መንገዶች ነበሩ።
ለምሳሌ፣ እስክንድር ስልኩን ሊያምጣላት ወጣ እንዳለ ስልክ ይደወልላታል፣ እንበል። እስክንድር ፈጠን ብሎ ይመለስና ስልኩን ከሰጣት በሁዋላ ብርጭቆውን አንስቶ ይጎነጨል። ፍሬ ፣ ይቅርታ ትጠይቀውና ደዋይዋን ለማናግር ትወጣለች።

ተሾመ
እኔ ነኝ ፍሬሰለም፣ አንድ ነገር ልነግር

ፍሬ እየተርበተበተች
እንዴት አሁን ትደውልልኛልሀ። ከሱ ጋር ነኝ።

ተሾመ
አውቃለሁ።

ፍሬ
ታውቃልሀ ? እኔንም ትከታተለኛለሀ ማለት ነው።

ተሾመ
ስራ ኮ ነው። ስለ ክኒኑ ላስጠነቅቅሽ ነው።

ፍሬ (በቀስታ )
ምንድን ነው የምታስጠነቅቀኝ። አድርጌለት እየጠጣው ነው። አሁን ይተኛል።

ቴሾመ
የደበቅንሽ ነገር አለ። ክኒኑ የሚያስተኛ ሳይሆን

ፍሬ
ም ምን

ተሾመ
አሁን ዝም ብለሽ ስሚ። ቁዋንጣ ሆኖ ስለሚያድር እቃውን ይዘሽ በለሊት ውጪ።

ፍሬ
ምን ? አ ?

ስልክ ይዘጋል። ፍሬ እየተርበተበተች ወደ ስክንድር ትመለሳለት። አጅሬ የመጀመሪያውን ብርጭቆ ጨርሶ ሁለተኛውን አጋምሶአል።

ፍሬ
ይቅርታ ስክንድር እዚህ መቆየት አልችልም። አዝናልሁ።

ስክንድር
ምን ነው፣ በደህና ?

ፍሬ
የደረሰኝ መልእክት ጥሩ ስላልነበር ብቻዬን .........
ብላ ወደ ክፍሉዋ።

ከነ ተሾመ ጋር ስትጨቃጨቅ ቆይታ፡ አንድ ሰዓት በሁዋላ ትመለሳለች። በፍርሀት እየንተቀጠቀች በሩን ገፋ ስታደርገው ይበረገጋል። ስክንድር አልጋው ላይ የለም። ገባ ስትል ወለሉ ላይ ተዘርሮ ታየዋለች። አይንቃነቅም። አይኑ ጣራው ላይ ተተክሎአል። ትደነግጣለች። እያማተበች ቀስ ብላ ወደ ውስጥ፣ ቦርሳው ያልበት ላይ እያማተረች። ወደ ቦርሳው ስትራመድ ስክንድር ቀና ይላል።

ስክንድር
ፍሬሰላም መጣሽ፣ እንቅልፍ እንቢ ሲለኝ ወለል ላይ ተዘርግቼ ሜዲቴሽን ያዝኩ። (ብሎ ብድግ፣ )

ፍሬሰለም (ሙት መንፈስ እንዳይች ነገር ትንፋሽዋ ምንድግ፣
እንቅልፍ እንቢ ሲለኝ ?

ስክንድር
ቪኖው እኮ የባሰ አነቃኝ

ፍሬ
እ ? አነቃኝ ?

ስክንድር
እህ። ቀንጆ ቪኖ ነው። ማጅራቴን ሁላ ጭብጥ አድርጎኝ የነበረው ለቀቀኝ።

ይህ እንግዲህ ተመለካቹን የተለያየ ትያቄ በውስጡ እንዲያብሰለስል ነው። ቁዋንጣ ሆኖ ያድራል ያልነው ሰው፣ የባሰ ነቅቶ ቁጭ ማለቱ።
ዶ /ር ብሌን አደገኛውን ክኒን በተራ የራስምታት ክኒን መቀየሩዋን በሁዋላ እናውቃለን። ሰ ፊ እንደዚ ማድረግ ነበረበት ማለቴ ሳይሆን ልብ ማንጠልጠል በሚቻልበት ትይንት ሁላ ዘዴውን መጠቀም ብሽቁን ፊልም ሳይቀር ከሞት ያድናል ለማለት ነው።

2. የዶ /ር ብሌን ግድያ ትይንት እንመልከት
የዶ /ር ብሌን ግድያ ሙክራ ከግማሽ ደቂቃ በላይ አልወሰደም። ገዳዩ ሲገባ ብሌን በቀጥታ

ኤሊቬቴር ውስጥ ትገባለች። ጥሩ መግደያ ቦታ ውስጥ። እዚያ ጠብሶአት ውልቅ ይላል። አለቀ። ልብ ሰቀላ የለ ምን የለ። ግድያ እንዲያ ተመቻችቶ አይጠናቀቅም። እንኩዋ ገድሎ ለመውጣት የሰላም መልእክት ለሰው ለማድረስ እንኩዋን ስንት ችግር አለ። አይደል እንዴ ሄሮን ? ስራ ላይ ናቸው፣ አልገቡም፣ አሁን ወጡ፣ አይደል እንዴ የምንባለው ?

እና እዚህ ላይ ጥሩ ልብሰቀላ መጠቀም ይቻል ነበር ባይ ነኝ። ዶክተርዋ ኦፔረሽን ላይ ሆና ገዳዩ እስክትወጣ እንኩዋ ሲጠብቅ ብናይ ሰቀላ ነው። ከሰው ጋር ሆናበት ሲከተላት ብናይ። አልመች ሲለው ሲያስጠራትና እንደ ደህና ሰው ጭር ወዳለ ክፍል ተያይዘው ሲሄዱ ወዘተ ብናይ። ተመልካቹ ቢለንን ማስጠንቀቅ ከማይችልበት ቦታ መሆኑ ራሱ የሚፈጥረው የቁጭት ስሜት አለ። በዚህ ላይ ከቢለን መሞት በተጨመሪ፣ ሌላ የሚጎዳ ሰው እንዳለ ብናውቅ ሰቀላው ይመጥቃል። ለምሳሌ በዚህ ወሳኝ ወቅት የብሌንን ቀጥተኛ የህክምና እርዳታ የምትጠብቅ የስምንት አመት ልጅ፣ ኦፔሬሽን አልጋ ላይ ተንጋላ ብናይ፣

3. የሆቴሉ አስተናጋጅም በቀለሉ ነው፣ የተገላገለው። እሱም ብቻውን ክፍል ውስጥ እያለ ያለ አንደች ግም ግም ግድያው ይጠናቀቃል። አይስብም።
እዚህ ትይንት ውስጥ ልክ እንደ ብሌኑ ጥሩ ልብ ሰቀላ መጠቀም ይቻል ነበር። ለነግሩ አስተነጋጁ የእስራኤል ግርፍ ኮማንዶ እንደሆነ ተነግሮን ስለነበር እዚህኛው ትይንት ላይ መጀመሪያ ሁለቱ ሊገዳደሉ ሲሩዋሩዋጡ፣ ሲደባበቁ፣ ሲፈላለጉ፣ ሲታኮሱ ማሳይት፣ ከዚያ እንደምንም ወደ ጨበጣ አሽጋግሮ አስተነጋጁ ገዳዩን በካራቴ መፈጠሩን እስኪጠላ ቢወለውለው፣ በመጨረሻ እያዳፋ ለፖሊስ ቢያስረክበው ተመለካች በበቀል ይረካ ነበር።

4 . እነተሾመ ፍሬን ሊይዙ ሲሄዱ የነበረው ውጥረት ልብ የሚሰቅል ነበር። በዚያው እስክንድርን የሚያሳድድ ሰው ቢኖር ሌላ ልብሰቀላ መፍጠር ይቻል ነበር። ወንጀል ነክ ፍልሞች በአብዛኛው የጎበዙንና የሌባውን (Hero vs Nemesis) የመጨረሻ ፍጥጫ (CONFRONTATION SCENE) አሳይተው ይጠናቀቃሉ። ስክንድርና ተሾመ የሚፋጠጡበት ሁኔታ ቢመቻች፣

5. ዶክተር ለማ ጥናቱ እጁ እንደገባ ሲያመልጥ ቢታይ ተመልካቹ ያብድ ነበር , እላልሁ።።። እዛ ምእራፍ ላይ ጥሩ የማጠቃለያ ልብ ሰቃይ ትይንት መስራት ይቻላል። ለማ ጥናቱን ይዞ ከአገር ለመውጣት ሲጣደፍ፣ እስኪነቃበት በስልጣኑ ብዙ ነገር ሲያመቻች ብናይ። አንዳንድ ዳይሬክተሮች እንዲህ አይነቱን ሌባ አይሮፕላን እስኪሳፈር ድረስ የተሳካለት በማስመሰል የተመልካችን ልብ ይሰቅላሉ።

በአጠቃላይ በየትይንት ነጥቡ (PLOT POINT) በተቻለ ልብ ሰቀላ መጠቀም፣ ልብሰቀለ ባለበት ላይ ደግሞ ሰቀላውን የበለጠ ለማንጠልጠልና ቆይታውን ለማራዘም መሞከር ይበጃል።

በሚቀጥለው ማጠቃለያ ይዤ ብቅ እለለሁ። እስከዛው የአገራችንን ፊልምና መጽሀፍ , ብሽቅም ይሁን አሪፍ ሁሉንም ገዝተን እናንብ፣ እንይ። ቢያንስ በዚህ መልኩ ለእድገቱ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማድረግ ይቻል ይሆናል። የጥበብ ስራዎችን መግዛት እንልመድ፣ በስጦታ መልክ ማበርከትም አንድ መንገድ ይመስለኛል። ያን ማድረግ ካልቻልን ኮፒ

ከመግዘት እንቆጠብ፣ መዋዋስም አናብዛ። ጉዋደኞቼን ገዝታችሁ እዩ ማለት ከጀመርኩ ቆይቻለሁ። እናንተስ ሄሮን፣ ዛዙ፣ ሳራንዴም፣ ባሻ፣ ዋናው፣ ብራንጎ ?

እረ ወደጄ ሾተልን እዚህ ክፍል አላየሁትም። እንዴ እንዴ ? በል ይህ ክፍል ሳይዘጋ የምትለንን በለን። በዚህ ዘርፍ ብዙ እንደምታውቅ እናውቃለን። ለምሳሌ በፊልም ስራ ድርብርብ ሀላፊነት ስለመያዝ እስኪ አውጋን።
ብራንጎም ብእርህን የሚገታው ነገር ያለ አይመስለኝም። እና ካንተም እንጠብቃለን። በነገራችን ላይ አሉላን ጨርሼዋለሁና የሆነ ነገር ሞጫጭሬ ላናድድህ አስቤአለሁ።

ፓስወርድ

---

ፓስወርድ

ማጠቃለያ ይዤ ብቅ እለለሁ። እስከዛው የአገራችንን ፊልምና መጽሀፍ , ብሽቅም ይሁን አሪፍ ሁሉንም ገዝተን እናንብ፣ እንይ። ቢያንስ በዚህ መልኩ ለእድገቱ አዎንታዊ እስተዋጽኦ ማድረግ ይቻል ይሆናል። የጥበብ ስራዎችን መግዛት እንልመድ፣ በስጦታ መልክ ማበርከትም አንድ መንገድ ይመስለኛል። ያን ማድረግ ካልቻልን ኮፒ ከመግዘት እንቆጠብ፣ መዋዋስም አናብዛ። ጉዋደኞቼን ገዝታችሁ እዩ ማለት ከጀመርኩ ቆይቻለሁ። እናንተስ ሄሮን፣ ዛዙ፣ ሳራንዴም፣ ባሻ፣ ዋናው፣ ብራንጎ .

እረ ወደጄ ሾተልን እዚህ ክፍል አላየሁትም። እንዴ እንዴ ? በል ይህ ክፍል ሳይዘጋ የምትለንን በለን። በዚህ ዘርፍ ብዙ እንደምታውቅ እናውቃለን። ለምሳሌ በፊልም ስራ ድርብርብ ሀላፊነት ስለመያዝ እስኪ አውጋን።
ብራንጎም ብእርህን የሚገታው ነገር ያለ አይመስለኝም። እና ካንተም እንጠብቃለን። በነገራችን ላይ አሉላን ጨርሼዋለሁና የሆነ ነገር ሞጫጭሬ ላናድድህ አስቤአለሁ
ይሄ ከአስር ቀን በፊት የለጠፍኩት ነው። ተመልሼ ሳየው አንድም ዋርካዊ ድምጡን ሳያሰማበት ግምግሙ ጉዋዳ ተጎድጉዶ ሳገኘው ገረመኝ። Sad

ለመሆኑ አላችሁ ?

አንዳንድ የሳይበር መመዝገቢያ ፎርም ከተሞላ በኍላ , የሆኑ ፊደሎች ይሰጥና ተይባቸው ይላል . እውን ፎርሙን የሞላው ሰው መሆኑን ለማረጋግጥ .

እንደዚያ ማድረጌ ነበር . ስም ጠርቼ መቀስቀሴ .. አውን የሚያነብ መኖሩን ለማወቅ ,
Wink

ቆጣሪውስ ?

ቆጣሪውን አላምናውም . ከፍቶ የዘጋውንም ሁሉ ይቆጥራል , እሱ .

እና የፊልምና የመጽሀፍ ግምገማ ለጥቂት የሙያው ሰዎች በቀር ለሌላው ስሜት የማይሰጥ , አሰልቺ መጣጥፍ መሆኑን ስለተረዳሁ , እዚህ ላይ አበቃለሁ . በአጋጣሚው , ያነበባችሁኝንና ሀሳብ ያካፈላችሁኝን ሁሉ ከልብ አመሰግንናለሁ .

በተረፈ , በፊልሞችና በመጻህፍት የሚሰነዘር ሂስና ግምገማ ማንበብ የምትሹ , መቸም አንድ ሁለት አይጠፋም , አገር ውስጥ የሚታተሙ ወርሀዊ የባህል መጽሄቶችን አገላብጡ .

በቸር ያናብበን .

ፓስወርድ

ማለፍያ የሆነ ውይይት !

ይበል ብያለሁ , ይበል !

---

በፊልም ስራ ድርብ፣ ድርብርብ የሀላፊነትና የአምራር ቦታ ስለመያዝ

ፊልም / ሰማያዊ ፈረስ

ፕሮዲዩሰር /ሰራዊት ፍቅሬ
ዳይሬክተር / ሰራዊት ፍቅሬ
ደረሲ / ሰራዊት ፍቅሬ
መሪ ተዋኒ / ሰራዊት ፍቅሬ

ፊልም / ቀይ ስህተት

ፕሮዲዩሰር /ቴድሮስ ተሾመ
ዳይሬክተር / ቴድሮስ ተሾመ
ደረሲ / ቴድሮስ ተሾመ
መሪ ተዋኒ / ቴድሮስ ተሾመ

ፊልም / የተወጋ ልብ

ፕሮዲዩሰር / ቢኒያም ወርቁ
ዳይሬክተር / ቢኒያም ወርቁ
ደረሲ / ቢኒያም ወርቁ
መሪ ተዋኒ / ቢኒያም ወርቁ

ፊልም / የባህር በር

ፕሮዲዩሰር / ጥላሁን ጉግሳ
ዳይሬክተር / ጥላሁን ጉግሳ
ደረሲ / ጥላሁን ጉግሳ
መሪ ተዋኒ / ጥላሁን ጉግሳ

ፊልም፣ እንደ እግር ኳዋስ ጨዋታ የቡድን ስራ ውጤት ነው። የተዋጣ ፊልም ለመስራት ከበጀት ይልቅ የብዙ ባለሙያዎችን ልምድ፣ ክህሎትና ያልተቆተበ ጥረት ይጠይቃል። እውቀት፣ ብቃትና ታታሪነት ከሚጠበቅባቸው የፊልም ስራ ሀላፊዎች ቀደምቶቹና ዋናዎቹ ፕሮዲውሰሩ፣ ዳይሬክቴሩና፣ መሪ ተዋኒው ናቸው። እነዚህ ቦታዎች በአንድ ሰው ሲያዙ የፊልሙ ይዘትና አሰራር ላይ አሉታዊ አስተወጽኦ እንደሚኖረው ከላይ የተዘረዘሩት ሶስት ቆየት ያሉ ፊልሞችን ማየት ብቻ ይበቃል። የባህር በር በቅርብ የወጣ ፊልም ነው። እንደ ሌሎቹ፣ እራቱ ከፍተኛ የአመራር ቦታዎች በአንድ ሰው ስለተያዙ የሌሎቹን እጣ ፈንታ ከመጎናጸፍ ይድናል ብዬ አልጠብቅም። በእንድ የእግር ኳዋስ ቡድን ውስጥ የበረኛውን፣ የተርሲኒውን፣ የአከፋፋዩንና የአጥቂው ቦታና አንድ ሰው ይዞት ቢጫወቱ ቡድኑ መሳቂያ መሳለቂያ ከመሆን እንደማይድን ሁሉ፣ ፊልሞችም በአንድ ሰው ሲሰሩ የሚገጥማቸው እድል ያው ነው። በእንድ ሰው የተደረሰ ፊልም፣ በደራሲው ደሬክተርነት ሲሰራ ዴራሲው ሲጽፍ በአእምሮው ይቀረጽ የነበርውን ምስል ሊያሳይን ይፈልጋል፣ ይገደዳልም። በሌላ ዳይሬክተር ሲመራ ግን፣ ምንም ባልቀዳ አእምሮ ስክሪፕቱን ወደ ተንቀሳቃሽ ምስል መቀየር ስለሚሆን የተለየና በጣም የተሻለ ስራ እንድሚሰራ የፊልም ኤክስፐርቶች ይመሰክራሉ። ( በቀጣዩ ጽሁፍ shooting script አቅርቤ ለማብራራት እሞክራለሁ . የኛ ፊልም ሰሪዎች ይህን ተራ ነገር አያውቁትም ብዬ አልልም። ችግራቸው ግን ምን እንደሆን ማወቅ አልቻልኩም።

ትያትር / ውብ ሰይጣኖች
ፕሮዲዩሰር / ራእይ ጥበባት
ዳይሬክተር / ኢዛና ገርማ
ደራሲ / አቤል አብርሀም
መሪ ተዋኒ / ዮናስ ሀይሉ /ቤተልሄም በላይ

በእንድ ሰው ከሚሰራ ፊልም ይልቅ፣ እንደ ውብ ሰይጣኖች አይነት ብዙ ጠበብቶችን ያሳተፈ ትያትርን ለማየት እጉዋጉዋለሁ። የትየትሩ ዳሬክቴር በሰጠው መግለጫ የመድርክ ትያትር መምራት ምን ያህል አድካሚና እልህ አስጨራሽ መሆኑን ገልጾልናል። በዚህ ስራው ላይ የመሪ ተዋኒነቱን ቦታ ቢጨምርበት ተውኔቱ ምንኛ ይጎዳ እንድነበር መገንዘብ ከባድ አይመስለኝም። ውብ ሰይጣኖች የተዋጣለት ተውኔት እንደሆነ ተመስክሮለታል። የሀላፊነትና የአመራር ቦተዎች በተለያዩ ሰዎች መያዙ ለዚህ አዎንታዊ ውጤቱ ከፍተኛ እስተዋጽኦ እንዳለው በእርግጠኛነት መናገር ይቻላልና ከ 'ሳይጣኖቹ ' እንማር ለማለት ነው።

ፓስወርድ

የጽሁፉ ምንጭ . http://akamjirta.wordpress.com/

THE ETHIOPIAN CINEMA INDUSTRY

In no time ever before, these days the number of motion picture release is escalating. Let you go any cinema hall in Addis, you will see a Habesha Movie Poster on large billboard. Some years back people line up at cinema entrances for theatres but not these days. Now seems it is time for movie.

Every time a movie is released, you will hear the phrase " A movie that takes the cinema industry one step up" yet you may see some people leaving the hall five minutes after the movie is started. There are many incidents where in a single movie directing, screen play, acting, casting … might be done by a single person. This is, as I believe, a disaster to the industry' s growth. It is obvious that a person might be a multi professional but may not be a master mind in all the same time.

There are some movies that I consider as better work like SERIYET, YEWONDOCH GUDAY, ASHENGE, as having originality (These are not the only best if I should count).

It is really hard to find a real data concerning which movie is the leading income wise. I don' t know why any of them are afraid to tell the actual income they made from the movie, (the Inland Revenue or thieves, heaven knows why).

These days, if you want to go to any of the cinemas in Addis, you don' t have to bother any one, you just Google on the site: http://www.ethiojoy.com/ and make the choice.

————————————

ኃይሌ ገሪማ ስለ ኢትዮጵያ ሲኒማ እንዲህ ብሎ ነበር ::

ከሶስት አመታት በፊት ኢትዮጵያ ውሥጥ ሲኒማ አልተወለደም የሚል አቋም ነበረው ::
አሁንም ይህንን ሀሳቡን አልቀየረም ይሆን Question
password ምን ትላለህ Question

ሰራንደም

ሁሉም ነገር ከላይ ሆነው ሲያዩት ድፍጥጥ ይመስላል . ከታች ለሚያይ ደግሞ ሾጣጣ ነው . ብዙሀኑ ሲኒማ ተመልካች የሊቁን አባባል ይጋራል የሚል እምነት የለኝም . ኢንዱስትሪው "እንደጉድ " እየፈላ መሄዱን ስናይ ደግሞ በመዳህ ላይ ያለው ሲኒማ ቆሞ የሚራመድበት ጊዜ መቃረቡን እንረዳለን .

ጥያቄው እንዴት ነው ድርሻችንን የምንወጣው ይመስለኛል ..

በነገራችን ላይ , ካምፖራዳ የተሰኘው "አንግሎ አማርኛ ፊልም " አይተኸዋል ? በፊልሙ ታሪክ ላይ አጠር ያለ ሂስ ወርወር ስለማደርግ ሰሞኑን ብቅ ብለህ አንብበኝ .

ፓስወርድ

—————————————

password እንደጻፈ(ች)ው:

ሁሉም ነገር ከላይ ሆነው ሲያዩት ድፍጥጥ ይመስላል . ከታች ለሚያይ ደግሞ ሾጣጣ ነው . ብዙሀኑ ሲኒማ ተመልካች የሊቁን አባባል ይጋራል የሚል እምነት የለኝም . ኢንዱስትሪው "እንደጉድ " እየፈላ መሄዱን ስናይ ደግሞ በመዳህ ላይ ያለው ሲኒማ ቆሞ የሚራመድበት ጊዜ መቃረቡን እንረዳለን .

ጥያቄው እንዴት ነው ድርሻችንን የምንወጣው ይመስለኛል ..

በነገራችን ላይ , ካምፖራዳ የተሰኘው "አንግሎ አማርኛ ፊልም " አይተኸዋል ? በፊልሙ ታሪክ ላይ አጠር ያለ ሂስ ወርወር ስለማደርግ ሰሞኑን ብቅ ብለህ አንብበኝ .

ፓስወርድ

ሰላም ወንድም ፓስወርድ :: አንተ እንዳልከው የሀገራችን ሲኒማ በመዳህ ላይ ነው :: አልተወለደም ማለት እዚህ ደረጃ ያደረሱትን ሰዎች ሥራ እና ልፋት መካድ ነው ሚሆነው :: በቂ የሙያ እገዛ እና ልምዱ በሌለበት ሁኔታ አንዱ ከአንዱ እየተማረ ብዙ ለውጦች እያየን ነው :: ሆኖም በሀገሪቱ ውስጥ በሚድያ እና በሲኒማ ዘርፍ በፋካልቲ ደረጃ ብቃት ያለው ትምህርት ሚሰጥ ኮሌጅም ሆነ ዩኒቨርስቲ ባለመኖሩ የፊልሙ እድገት ባለበት እንዲረግጥ አድርጎታል :: በቅርቡ ካፒታል ጋዜጣ ላይ እንዳነበብሁት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በዚሁ ዘርፍ እስከ ድህረ ምረቃ ድረሥ ትምህርት በቅርቡ መሥጠት እንደሚጀምር ነው ::

ሌላው ብዙ ፊልሞች ላይ እንደምንመለከተው አንድ ፊልም ስራ ላይ አንድ ሰው ድርብ ድርብርብ የኃላፊነትና የአመራር ቦታ በሞኖፖል የመያዝ ችግር በበርካታ የሀገራችን

ፊልሞች ላይ እያስተዋልን ነው :: እኔ እንደሚመሥለኝ ለዚህ ችግር ዋናው መንሥኤ የበጀት እጥረት ነው :: ደራሲያን ይህንን ችግርን ለመቅረፍ ሲሉ በትወና በማዘጋጀት .......ወዘተ ቦታ ላይ እናያቸዋለን :: ይህ የወጪ ቁጠባ አባዜ ዋናውን ተዋናይነት ድርሻ እስከመጫወት ያደርሳል :: አንዳንድ ደራሲያን እንደ ምክንያት ሚያቀርቡት ፊልሙን ዳይሬክት ሚያደርግላቸው ሰው እንዳላገኙ : አንዳንዴ እነሱ እንደ ሚፈልጉት ሚሰራላቸው ሰው / ተዋናይ / እንዳጡ የመሳሰሉትን ምክንያቶችን ሲደረድሩ እንሰማለን ::

ፓስወርድ ካምፓራዳ ያልከው ፊልም መቀሌ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የዶርም ህይወት ላይ ሚያጠነጥን ፊልም ነው እንዴ Question እሱ ከሆነ አይቼዋለሁኝ :: ከተሳሳትኩ አርመኝ ፊልም አርእስት በማስታወስ ሰነፍ ነኝ :: Embarassed ለማንኛውም ስለ ፊልሙ ምትለውን ለማንበብ በጉጉት እጠብቃለሁኝ ::

ከላይ የጻፍኩትን ፖስት ካደረኩኝ በኃላ አንድ ጥቅምት 2000 የወጣች ሮያል መጽሄት አገኘሁኝ :: እዚህ መጽሄት ላይ የአርቲስት ታምሩ ብርሀኑ ቃለ -መጠይቅ አለ :: ለውይይታችን ማጠናከርያ እንዲሆን በማሰብ የእርሱን ቃለ -መጠይቅ በቁንጽሉ አቀርበዋለሁኝ ::

Question Arrow በሀገራችን የፊልም ጥበብን የሚያስተምር ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በሌለበት ሁኔታ የፊልም ጥበብ ተጀመረ ማለት አይቻልም የሚሉ ወገኖች አሉ :: ይህንን አስተያየት ትቀበለዋለህ ?

ታምሩ :- የፊልም ጥበብ አልተጀመረም ማለት ያስቸግራል ::አይ በቃ !...እዚህ ደረጃ ላይ ደርሰናል ለማለትም ያስቸግራል :: ግን እየሰራን ነው :: የሀገራችን የፊልም ጥበብ ጥሩ ደረጃ ላይ ነው ያለው :: በነዚህ ቅርብ አመታት ውስጥ ሚታዩት ለውጦች ጥሩ ናቸው ::ስርየት የሚለውን በጣም ጥሩ የሆነ ፊልም ነው :: እነዚህ ፕሮዳክሽኖች በወጡበት ሃገር ፊልም አልተሰራም ብለህ ለማሰብ ከባድ ነው :: እንዴት አልተሰራም ? ...የተሰሩትስ ? የተሞከሩትስ ?

Question Arrow ደካማ ፊልሞችስ የሉም ?

ታምሩ :-ሊኖሩ ይችላሉ :: ከተሰራ ምንጊዜም ስህተት ይኖራል :: ካልተሰራ ነው ሥህተት የሌለው ::.....ጭራሽ ፊልም አልተሰራም የሚለውን ነገር በበኩሌ አልቀበለውም :: ሌላው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ይህንን ችግር አጥንቶ የፊልም ጥበብ የሚያስተምር ተቋም ለመክፈት ዝግጅቱን ያጠናቀቀ ይመስለኛል ::....በትምህርት በታገዘ ሁኔታ ሲሰራ ደግሞ የበለጠ የሚያድግ ይመስለኛል ::

Question Arrow የአንድ ሰው ደራሲ :የፊልም ዳይሬክተር : ተዋናይ መሆንና መሥራት ጥሩ ነው ?... በአብዛኛው የሃገራችን ፊልሞች ደራሲው : ዳይሬክተሩ : ተዋንያን መዳቢው : ኤዲት አድራጊው አንድ ሰው ነው :: ተዋናይ ሆነው የሚሰሩም አሉ :: ዳይሬክተር ሆኖ መተወን አስቸጋሪ አይሆንም ?
ታምሩ :-እውነት ነው !... ምንም ጥያቄ የለውም :: አንዳንዴ አንድን ሥራ ራሴ ዳይሬክት

ላደርግ የምችልበት ሁኔታ አለ :: ለራስህ ድርሰት ቅርብ ሥለሆንክ ታውቀዋለህና ራሴ ዳይሬክት ባደርገው የሚል ስሜት ውስጥህ ይኖራል :: ከዚህ አንጻር ነው እኔ ያየሁት እንጂ አንተ ያነሳከው ትክክል ነው :: እኔ ያልታየኝ ነገር ለሌላው ሰው ሊታየው ይችላል :: ወይም ደራሲው ጋር የተተወን ክፍተት ዳይሬክተሩ ሊያየው ይችላል ::

Question Arrow ጥሩ ከሆነ ለምን ተከፋፍሎ መሥራት አይቻልም ?

ታምሩ :-ከኢኮኖሚውም ከሌሎችም ነገሮች አንጻር አንድ ሁለት ሥራ መደረብ አንዳንዴ ምንም አይደለም :: አራት ...አምስት ሥራ ከሆነ የሚደረበው በእርግጥ ሊከብድ ይችላል :: ነጥሎ ለመሥራት ግን የኢኮኖሚውም ጉዳይ አለ ::